ለተከበሩ አቶ ደሴ ዳልኬ የክልሉ ፕሬዝዳንት

<u>አጭር መልእክት ከሲዳማ ብሔር</u>

## <u>መግቢያ</u>

ሲዳማ በባህሉ አንድ ሀገራዊ ወይም ሲከሰት በክስተቱ ዙሪያ መወያየት መመካከርና ክስተቱ በምንና እንዴት እንደመጣና በተከሰተዉ ክስተት ሳቢያ ምን ልመጣ እንደሚችል ይነጋገራል ይተነብያልም:: ይህ አጭር ጽሁፍ የሚያተኩረዉ በሺፈራዉ ሽጉጤ ከክልሉ ፕሬዝዳንትነት የመባረር ዜናን ተከትሎ በሲዳማ ብሔር ሲደረግ የነበረዉን ዉይይትና ከሱ መባረር በሃላ ምን መሆን እንዳለበት ሕዝቡ በተነጋገረባቸዉና በተስማማባቸዉ ጉዳዮች ዙሪያ የሚያጠነጥን ነዉ::

## <u>ክፍል አንድ ፡የሺፈራዉ ከክልል ፕሬዝዳንትነት የመባረር ዜናና የሕዝቡ ስሜት</u>

መቼም ጊዜ የማያመጣዉ ጆሮ የማይሰማዉ ጉድ የለምና በክልሉ በተለይም በድፍን ሲዳማ ብሔር ዘንድ በጣም ይጠላ የነበረዉ አዉሬዉ ሺፈራዉ ሽጉጤ ካለበት ሰይጣናዊ ዙፋኑ መባረሩን የሚያበስር ዜና ኢቲቭ አሰማን:: የአዉሬዉን መባረር የሰማዉ ሁሉ ዜናዉን በብርሀን ፍጥነት ለሁሉም እንዲሰራጭ አድርጎ በሚከተሉት ነጥቦች ዙሪያ ይነጋገርና ይከራከር ጀመረ:: ዉይይቱና ክርክሩ አሁንም ወደ ፍትም የሚቀጥል ሆኖ ዋና ዋና የዉይይቱ ነጥቦች የሚከተሉት ናቸዉ::

1ኛ/ ዋናዉና ትኩረት አግ ቶ በሕዝቡ ሰእየተገረመ ሲነጋገርበት የነበረዉ ተአምራዊ ጉዳይ ሺፈራዉ ከሲዳማ ምድርና ከሕዝቡ ፍት እንደሚወገድ የተነገሩ ሁለት ትንቢቶች በትክክል መፈጸማቸዉን ሲሆን ትንቢቶቹ የተነገሩት በሁለት አምልኮ ሥፍራ ሲሆኑ አንደኛዉ ትንቢት በሲዳማ ባህላዊ አምልኮ ቅዱስ ከሆነዉ ከሐዋሳ ጉዱማሌ ሲሆን ሁለተኛዉ ትንቢት በፕሮቴስታንት ሃይማኖት ቅዱስ ሥፍራ ከሆነዉ ከቤተክርስቲያን ነዉ :: አንደኛዉን ትንቢት በተመለከተ የሲዳማ ብሔር የ2004 አዲስ አመት መባቻ ፍቼ ክብረ በአሉን እንደተለመደዉ በብሔሩ መናገሻ ከተማ በሐዋሳ ባለዉ ጉዱማሌ ተሰብስቦ የበአሉ ሥነ ሥርአት በሲዳማ ሃይማኖት መሪ ጭሜሳዎች መጀመር ስላለበት ጭሜሳዎቹ ሥነ ሥርአቱን ፈጽመዉ ልመርቁ ወደተመደበላቸዉ ሥፍራ ሲያመሩ በማንነቱና በአስተዳደጉ ራሱን አናሳና ትንሽ አድርጎ በበታችነት መንፈስ ተዘፍቆ የኖረዉ ትንሹና የበታቹ ሺፈራዉ እድሜ ለኢህአደግ ከአመድ ተነስቶ ዙፋን ላይ ፍጥጥ በማለቱ ማንም ሰዉ በማንኛዉም ቦታ ከሱ ፍት የማንም ሰዉ ስም ማንሳትና አንዳች ነገር ማድረግም ዙፋኑን የቀማዉ ያህል ስለሚያናድደዉና ስለሚያስፈራዉ በእለቱም ይህ ሰይጣናዊ ቅናቱና ትዕብቱ ወጥሮት ቀድሜ መናገር ያለብኝ እኔ ነ ና

ጭሜሳዎቸ ይቀመጡ ሲል አብረዉት የነበሩት ካድሬዎች ለሺፈራዉ ሥነሥርአቱን ቀድሞ በምርቃት መክፈት ያለባቸዉ ጭሜሳዎች ናቸዉ; እስካሁን ሲደረግ የነበረዉ ይሄ ነዉ; ሲሉት ትንሹ ሺፈራዉ "የምን ጭሜሳዎችን ወይም የምን ሽማግሌዎችን ምርቃት ነዉ የምታወሩት ሲደነፉ ካድሬዎቹና ቅርብ የነበሩ ሰዎች ጭምር ሰምተዉ ሲበሳጩ ክርክሩ ትንሽ ጊዜ ወስዶ ነበርና የሰማዉም ላልሰማዉ አዳረሰ:: በጉዱማሌዉ ተሰብስቦ የነበረዉ 1,2 ሚሊየን የሚበልጥ ሕዝብ ሕፃን, ወጣት, ጎልማሳና ሽማግሌ ሳይቀር የትንሹን ድፍረት ሰምቶ ጉድ አለ:: ትዕግስቱም ተማጠጠ:: አናሳዉ ሺፈራዉ የካድሬዎቹንም ምክር አልሰማ ብሎ ማይክራፎኑን ከመድረክ መሪዉ በሃይል መንጭቀ ወስዶ በቅዱሱ ሥፍራ የብሔሩ ክቡራን ጭሜሳዎችን ዘለፈ ሰደበ ,አዋረደ:: በጭሜሳዎቹ መዘለፍና መዋረድ እሳት ጎርሶ እሳት ለብሶ ሲጠባበቀዉ ለነበረዉ የበአሉ እድምተኛ ሺፈራዉ "Ayiidde Cambalaalla" ሲል ሕዝቡም በአንድ ድምፅ "Iillitooti, አያድርስህ" ሲለዉ ጆሮዉን ተጠራጠረና እንደገናም ለAyiidde Cambalaalla ጨኼቱ ያዉ Iillitooti አያድርስህ ጩሄት ከቅድሙ ከፍ ብሎ አስተጋባ:: ጆሮዉን ባለማመን ደገመዉ ደጋገመዉ:: የሕዝቡም Iillitooti አያድርስህ እርግማን ከሐዋሳ አልፎ በሲዳማ ምድር ሁሉ አስተጋባ:: አናሳዉ በሕዝቡ ቁጣ ራደ, ተንቀጠቀጠ, ግፍቱም ፈላበት:: ተሽመድምዶ ልወድቅ ሲንገዳገድ አጃቢዎቹ ተሸክመዉት ወደ መኪናዉ ሲወስዱት ጭሜሳዎቹ ሕዝቡን ጸጥ እንድል ምልክት ሰጡና በባህሉ መሰረት ከፍተኛ ደረጃ ለደረሰ ባለጌ ሰዉ በሚረግሙት እርግማን ጭሜሳዎቹ የክብር ካባቸዉን ቡሉኮ እያራገፉ "አንተ ባለጌ በዚህ በቅዱስ ሥፍራ ስላዋረድከንና ቅዱሱን ሥፍራ በመዳፈርህ የዚህ ቅዱስ ሥፍራ አምላክ ያዋርድህ! ከሲዳማ ምድር ይንቀልህ! ለሚቀጥለዉ አመት (2005 ፍቼ በአል አያድርስህ! ከሲዳማ ሕዝብ መሃል ያዉጣህ!" በማለት ረገሙት:: እነሱን እየተከተለ እድምተኛዉ ሁሉ እርግማኑን አዝጎደጎደዉ:: እሱም ከሕዝቡ በመብረቅ ድምፅ በበለጠ እየተሰማ ያለዉን የእርግማን ድምፅ እየሰማ በድንጋጤ ተዉጦ በአጃቢዎቹ ትከሻ ላይ ሆኖ ወደ መኪናዉ ሲሸ ሕዝቡ በአሉን ማክበሩን ቀጠለ:: እግዚኦ ማረነ የሐዋሳዉ ቅዱስ ጉዱማሌ!! ይሄዉና ትንሹ ሺፈራዉ የ2004 ፍቼ ዉርደቱን በ2005ቱ ፍቼ ቀን ሕዝቡን ለመበቀል በሐዋሳ ከተማ ፀጥታ መምሪያ የራሴ ነዉ የሚለዉን ጄኔራል ከጦር ግንባር አምጥቶና በሲዳማ ዞን ፀጥታ መምሪያም እንደዚሁ ግዳጁን በትክክል ይወጣል በማለት የሚተማመንበትን በመሾምና በሱ ቀጥታ አመራር ለሚታዘዘዉ የልዩ ሃይልና ፌዴራል ፖሊስና የመከላከያ ጦርም ለእገዛ በተጠንቀቅ እንድጠብቅ ለፍጅቱ ሁለንተናዊ ድጋፍ አሰባስቦና ዝግጅቱን አጠናቆ እለቱን በጉጉት ሲጠባበቅ አቤት እግዚኦ የጉዱማሌዉ አድባር! እግዚኦ ንጹሃኖችን ከእልቂት ለመታደግ በሁሉም ሥፍራ የሚዘዋወረዉን የሞት መልዕክተኛ ዲያቢሎስን የምትገስጽ ቅዱስ መንፈስ እግዚኦ! እግዚኦ! እነሆ የሳጥናኤል ቁራጭ ሺፈራዉ የሲዳማን ምድር በደም ጎርፍ ልሞላ የ2005 ፍቼ በአል ቀንን ሲቆጥር እነሆ ለዳግም ሎቄ;

ሂሮሽማና ናጋሳኪ ጭፍጨፋ 20 ቀናት ብቻ ሲቀሩት ለአመታት በሌሎች የተለያዩ ሥፍራዎች በተለያዩ አጋጣሚዎች በግልና በጋራ ሲረግመዉ ሳይደርስበት የቆየዉ እርግማን እነሆ በቅዱሱ ሥፍራ በጉዱማሌ የጮሁት የጭሜሳዎቹና የሕዝቡ እርግማን አናሳዉን ከሲዳማ ምድረ ገጽ ላይመለስ ለዘለአለሙ ነቀለዉ :: አቤት እግዚኦ ማረነ ጉዱማሌ!! አሜን::

ሁለተኛዉ ትንቢት የተፈጸመዉ በአርበጎና ወረዳ ካሉት የፕሮቴስታንት አብያተ ክርስቲያናት ዉስጥ በአንዱ የሚያገለግል ነቢይ ያስተላለፈዉ መልዕክት ነዉ:: ይሄኛዉ ትንቢት የተነገረዉ በ2005ቱ የአካባቢ ምርጫ ማግስት ሲሆን የተፈጸመዉም ትንቢቱ በተነገረ በሁለት ወራት ዉስጥ ነዉ:: ጉዳዩ እንዲህ ነዉ:: አናሳዉ ሺፈራዉ በራሱ ይሁን ወይም ለራሳቸዉ ስትራቴጂ የሱን በአደባባይ መዋረድ የፈለጉት የበላይ አለቆቹ አዘዉት ይሁን አይታወቅም ለምርጫ ቅስቀሳ ብሎ ከ2 ሺህ በሚበልጡ ጦር ሰራዊት እየታጀበ በየወረዳዉ ሲዞር ነበርና ከሄደባቸዉ ወረዳዎች አርበጎና አንዱ ነበር:: ከተወለደበትና እናንተን ስለጠቀምኩ ተጠላሁ ተገደልኩ እያለ በጣም ጥቂት ከ10 በማይበልጡ ስግብግቦች አማካይነት እየዘላበደና እየወሸከተ ጎሳን ከጎሳ የሚያጋጭ ሴራ ሲዶልት ለተወሰኑ ጊዜያት ታግሶት የነበረዉ ሕዝብ እሱንና ደላላዎቹን ጭምር አንቅሮ ከተፋዉ የትዉልድ ወረዳ ሕዝብ ጭምር “በአደባባይ ሲዳማን ስትጨፈጭፍ ሲታራቁት ከመንግስት ስታጣላ በዘረጋሄዉ የሐሜትና የዉሸት ሰንሰለት የታላላቅ ምሁራኖችንና ታዋቂ የሀገር ሽማግሌዎችንና ባለሀብቶችን መልካም ስምና ዝና ስታስጎድፍ ጎሳን ከጎሳ ወረዳን ከወረዳ ስታባላ የሕዝቡን ሁለንተናዊ መብትና ጥቅም ስታጠፋ ምሁራን ልጆቹን እንደ ቡዳ ስትበላ ወዘተ እስካሁን የታገስንህ ይበቃሃልና ከፍታችን ዞር በልልን” እየተባለ ተዋርዶ ሲሸሽ እሱም “ሕዝቡን ዋጋችሁን ታገኛላችሁ ከዚህ ከረገጥኩበት አፈር በታች አስገባችሃለሁ” እያለ እየዛተ ሲሸሽ ነበር:: በአርቤጎና ወረዳም ተመሳሳይና እንዲያዉም የባሰ ተቃዉሞ ገጠመዉ:: ሕዝቡ የሲአንን የመወዳደርያ መለያ ምልክት የሆነዉን አዉራ ዶሮ በወረቀት ላይ ካለዉ ምስል በተጨማሪ አዉራ ዶሮዉን ከነነፍሱ ይዞ ጠበቀዉ:: በዚህ አድራጎት በንዴት የጦፈዉ አናሳዉ በሌሎች ወረዳዎችም ሲያደርግ እንደከረመዉ የዛቻና የማስፈራርያ ናዳዉን አዉርዶ በሲዳማ ባህል እጅግ ነዉርና አስጸያፍ በሆነዉ ስድብ Gojaamma (ፈልፈላዎች) በማለት ለስብሰባዉ ተጠርተዉ በመጡት አዛዉንቶች ፍት ሕዝቡን በጅምላ ሰደበ:: አረከሰ:: በባህሉ መሰረት Gojaamo (ፈልፈላ) ተብሎ የተሰደበ ሰዉ ወይም ጎሳ Gojaamo (ፈልፈላ) ያለመሆኑን በባህሉ መሰረት በሚመለከተዉ ጭሜሳ ሸንጎ ተረጋግጦለትና የመንጻት ሥነሥርአት ሳይደረግለት ቤት አይገባም; ከሌላዉ ሰዉ አይቀላቀልምና ድፍን የወረዳወ ሕዝብ ሺፈራዉ Gojaamma (ፈልፈላዎች) ብሎ በአደባባይ ከሰደባቸዉ ሰአት ጀምሮ የወረዳዉ ሕዝብ ቤቱ ሳይገባና ከሌላዉ ሳይቀላቀል በዚህ ስርአት ተጠምዶ ነበርና የዚህን ዉጥረት የሰማዉ ሰባኪዉ ነቢይ በሕዝቡ ሁኔታ ልቡ ተነክቶ “ለሕዝቡ ጭንቀት ምን ትለኛለህ? ምን ብዬስ ላፅናናቸዉ? ብሎ በፆምና

ጸሎት አምላኩን ሲማፀን የነሙሴ አምላክ እጅግ በጣም በፈጠነ ቅጽበት ለባሪያው መልስ ሰጠ:: ለሕዝቡም እንዲህ ብለህ መልዕክቴን ንገራቸው አለው:: ባሪያውም በሺፈራው ስድብ ቤቱ ሳይገባ መላ እየፈለገ ላለው ሕዝብ "ፈርኦን የእስራኤልን ሕዝብ በባርነት ሲያስጨንቅ በሙሴ አማካይነት ሕዝቡን የታደገው የሰራዊት ጌታ እንዲህ ይላችሃልና ስሙኝ! ከእንግዲህ በአደባባይ ያዋረዳችሁና የዛተባችሁ ሺፈራው በሐምሌ ወር (ያኔ ወሩ ግንቦት 2005 ነበር) ከፍታችሁ ገለል ይደረጋል! ከሲዳማ ምድር ይነቀላል! ከእንግዲህ የሲዳማን ሕዝብና ምድር አያይም!" በማለት መልእክቱን አስተላለፈ:: ሕዝቡም ሰምቶ "እስቲ እናያለን" ብሎ ዝም አለ:: የትንቢቱ ወሬ ከመቅጽበት በመላው ሲዳማ ምድር ተሰራጨ:: ነቢዩ መልዕክቱን ባስተላለፈ ሌሊት በሺፈራው አፋኝ ቡድን ታፍኖ ተወስዶ 24 ሰአት በማይሞላ ጊዜ ዉስጥ ፈርደዉበት ዘብጥያ አወረዱት:: የሲዳማ አምላክ በባሪያው አማካይነት ለሕዝቡ የገባዉን ቃል ኪዳን ትንቢቱ ይፈጸማል ተብሎ በተነገረ በሐምሌ ወር የሐምሌ ወር በገባ በመጀመሪያ ሳምንት ተፈጸመ:: ሕዝቡ ተአምር አለ:: አምላኩን አመሰገነ:: የምስጋና ፕሮግራም በየቤቱ ተደረገ:: እየተደረገም ነው:: አቤት እግዚኦ ለሰራዊት አምላክ!!

2ኛው የውይይቱ ነጥብ አውሬው ሺፈራው ሽጉጤ በየጊዜው ከሚቀያይራቸው ግልገሎቹ ጭምር በሕዝቡ ዘንድ የተተፋው ከግንቦቱ 16/1994 የንፁሃን ሰላማዊ ሰልፈኞች በክልሉ ባለሥልጣኖች እቅድ አውጪነት በሺፈራውና በግልገሎቹ ዋና ተዋናይነት በሎቄ በጠራራ ፀሃይ ከ350 በላይ ሕፃናት ተማሪዎች ደብተራቸዉን እንደታቀፉና በሎካ አባያ ደግሞ ሽማግሌዎችንና አሮግቶችን ከነጎጆ ቤቶቻቸው በማጋየትና ሬሳ ጭምር እንዳይነሳ በማስከልከል ፀረ ሲዳማና ፀረ ሕዝብነቱን በይፋ ካስመሰከረበት እለት ጀምሮ እስከዚች ደቂቃ ድረስ ለመስማትም የሚቀፉ ተዘርዝረው የማያልቁ ኢሰብአዊና አረመኔያዊ ጭፍጨፋዎችን; ጅምላ እስራቶችን; ዘረፋና ስርቆት ወዘተ ሲያደርግ አንድም ቀን ሕዝቡ የኔ ነው ብሎ ያልተቀበለዉንና በገባበት እየገባና በወጣበት እየወጣ ሲቃወመዉና ሲያጋልጠው በመንግስት በኩል ምንም ምላሽ ሳይሰጥ ተከርሞ ለምን በዚህ ወቅት ተባረረ? ሆነም ቀረም ከዚህ መባረሩንና ፌዴራል መግባቱን ሺፈራዉም አይፈልገዉም:: የመንግስትም የኢህአደግም ምርጫም እቅድም አይሆንም:: ሺፈራው ከዚህ ፕሬዝዳንትነት ወንበርህ ተነስተህ መንግስተ ሰማያት ከኢየሱስ ጎን ካለው ወንበር ናና ተቀመጥ ብሉት ለአንድም ቀን ቢሆን በፕሬዝዳንትነት ወንበሬ ላይ ተዉኝ እንደምል ምንም ጥርጥር የለዉም:: ስለሆነም ሺፈራው ከዚህ የተነቀለው በሲዳማ ሕዝብ ትግል መሆኑ ሐቅ ነው:: ኢህአደግ የሲዳማ ሕዝብ በሺፈራው ላይ ሲያሰማና ሲያሳይ የከረመዉን ተቃዉሞና ጥላቻ ለነሱ ቤት ሥራ ማሳካት ስለተመቻቸው ብቻ 6.7 ሚሊዮን ሕዝብ አቤቱታ ምንም ደንታ ሳይሰጠው ለአመታት የተሸከመዉን ሺፈራው ልያባርር የተገደደው የሲዳማ ሕዝብ በ2005ቱ የአካባቢ

ምርጫ ለምርጫ ቅስቀሳ በሺዎች በሚቆጠሩ ፖሊስና መከላከያ ሰራዊት ታጅቦ ሀዋሳ ከተማን ጨምሮ በ30ዉም ወረዳዎች ሲዞር አንድም ወረዳ አንድም ደጋፍ ሰዉ ሳይኖረዉ ሕዝቡ በአንድ ድምፅ እያወገዘዉ ያን ሁሉ ሰራዊት አስከትሎ እያለ በዉስጡ ያለዉ ሀጢአት; ድፍረትና ወኔ አሳጥቶት ተዋርዶ ሞባይሉን ሁሉ ጥሎ በጠራራ ፀሐይ ሲሸሽ የተቀረፀዉ ምስል በየቀኑ ለአለም ሕዝብ ሲተላለፍ ነበርና ኢህአደግ የሲዳማ ሕዝብ በሺፈራዉ ላይ ለመጨረሻ መጨረሻ ጊዜ መቁረጡን በመገንዘብ እንዳባረረዉ የአደባባይ ምስጢር ነዉ::

3ኛ/ በአንድ ሺፈራዉ መነሳት ብቻ የሲዳማን ሕዝብ አረካሁ ብሎ መንግስት የሚያስብ ከሆነ አንድን ሕፃን በከሬሜላ ከመደለል ያነሰ ጨወታ ነዉ በማለት ሕዝቡ ተነጋግሮ ደምድሞታል:: መንግስት ከሲዳማ ጋር ለመታረቅ ከፈለገ በሐምሌ 7/1997 በክልሉና በፌዴራሉ ሕገ መንግስት መሰረት በሲዳማ ምክር ቤት ፀድቆና ዉሳኔዉ ሕገመንግስታዊና ሁሉንም መስፈሪቶች ያሟላ ስለመሆኑ በ1997 መጨረሻ ላይ የተሰበሰበዉ የክልሉ ምክር ቤት በአጀንዳነት ተነጋግሮ ያፀደቀዉና ስለዉሳኔዉ ሕገመንግስታዊነትና ሲዳማ ከክልል መንግስትነት ባሻገር በሁሉም መስፈርቶች ራሱን የቻለ ብሔራዊ ሀገር መሆን የሚችልና መሆንም የሚገባዉ ሕዝብ ስለመሆኑ ከሀገር አልፎ ለአፍሪካና ለአለማችን ታላላቅ አስተሳሰብና ራእይ የነበራቸዉ (ነፍሳቸዉ በሰላም ትረፍና) ታላቁ ባለራእይ ጠቅላይ ሚኒስትር ክቡር መለስ ዜናዊ ጥር 11/ 1998 የሲዳማን ምሁራን በቤተ መንግስታቸዉና የካቲት 17/1998 የሲዳማን የሀገር ሽማግሌዎችን በቀያቸዉ በሐዋሳ ከተማ የሲዳማን የክልል መንግስትነት ዉሳኔን በተመለከተ ባነጋገሩበት ወቅት የመሰከሩት እዉኔታ ተቀርጾ በማስረጃነት አለ:: ሲዳማ ለዚህ ዉሳኔ ተግባራዊነት ብዙ የነፍስና የኢኮኖሚ ድቀት ዋጋ ከፍላል:: እየከፈለም ነዉ ::ወደፍትም ለመክፈል ሆድ ዉስጥ ካለዉ ጽንስ እስከ አዛዉንት ድረስ በሴራዉ መክሮ ዘክሮ ምሎ ተማምሎ ትግሉን በሁሉም አቅጣጫ እያፋፋመ ነዉ:: ስለሆነም የሲዳማ የክልል መንግስትነት ዉሳኔዉ በሀገሪቱ ሕገመንግስት እስካልተመለሰና በግንቦት 16ቀን 1994 ሰላማዊ ሰልፈኞችን በሎቄና በሎካ አባያ ደግሞ ሕፃናትንና አሮጊቶችን ከነጎጆአቸዉ በማጋየት በዚህ አሬመኔያዊ ጭፍጨፋ የተሳተፉትና ከዚያም በሃላም ቢሆን እስከዚች ደቂቃ ድረስ ንፁሃን ሲዳማዎችን በማስጨፍጨፍ; በጅምላ እስራትና አፈና; ሃብት ንብረቱን በመዝረፍና በማዘረፍ ወዘተ የተሳተፉት ሁሉ በሕግ እንድጠየቁ መንግሥት እርምጃ እስካልወሰደ ድረስ የሲዳማን ሕዝብ ድጋፍ አገኛለሁ ማለት ዘበት ነዉ::

4ኛ/ ሺፈራዉ የሚኒስትርነት ሹመት ወይስ የዘብጥያ ካቦነት ይገባዉ ነበር ለሚለዉ አጀንዳ ከፌዴራል ባለስልጣኖች አንዳንዶቹ ከሱ ጋር በጥቅም የተነካኩ ስለሆኑ ለሕግ ለማቅረብ አመነቱ እንጂ ሺፈራዉ ራሱም ቢሆን ለወህኒ ቤት ራሱን አዘጋጅቶ እንደነበር ዉስጥ አዋቂዎች

ይናገራሉ:: ከማንኛዉም ክልል በላይ ተንሰራፍቶ የሲዳማን ብቻ ሳይሆን የክልሉን 17.5 ሚልዮን ሕዝብን ከኢህአደግና ከመንግስት ያራራቀዉ ለሺፈራዉ ጉቦ አቀባባይነት በተመለመሉ የፍትሕና የፖሊስ ስርአት ሹመኞች በሚደርስበት ፍትህ መጓደል ሺፈራዉ በሱ ልክ መልምሎ ባስቀመጣቸዉ በክልል; በዞኖች; በከተማዎች; በወረዳዎችና ብሎም በቀበሌዎች መዋቅር በተሰገሰጉ ካቢኔዎችና ካድሬዎች አማካይነት ሲዘረፍ የነበረዉ መጠን ለሌለዉ የመንግስት ;የሕዝብና የነጋዴዉ ሕብረተሰብ ሀብት; ንብረትና ገንዘብ ሺፈራዉና በየእርከኑ ያሉ በሕዝብ ደም የተጨማለቁ ሙሰኞችና ምግባረ ብሉሹዎች በሕግ ካልተጠየቁ በተጀመረዉ ሀገራዊ የፀረ ሙስና ሕዝባዊ እንቅስቃሴ ላይ በተለይም በደቡብ ክልል ቀዝቃዛ ዉሃ የመጀለስ ያህል ነዉ የሚሆነዉ በማለት ሕዝቡ የሀ/ማሪያምን “ሙሰኞችን በቀጥታ ለኔ ንገሩኝ” ንግግሩን ማሞ ሌላ መታወቂያዉ ሌላ ብሎታል::

5ኛ/ ሺፈራዉ ሽጉጤ የተባረረዉ ለሕዝብ ተብሎ ከሆነ አንድ እሱ ብቻ ነዉ ወይ ሕዝብን ከመንግስት እንድቆራረጥ ያደረገዉ የሚለዉም ነጥብ ሌላዉ የመነጋገሪያ ርእስ ነበር:: ከየዞኖቻቸዉ በፀረ ሕዝብነታቸዉ ተተፍተዉ በዋሻነት በክልሉ ዴህዴን ጽ/ቤት; በቢሮዎችና ሌሎች መንግስታዊ መዋቅሮች ተሰግስገዉ ያሉ አለማየሁ አሰፋ; የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤትና የፍትሕ ፕሬዝዳንተችና ኦፍሴሮች እንዲሁም የፀረ ሙስና ኮሚሽንና የጠቅላይ አቃቤ ሕግ ሃላፍዎችና ኦፍሴሮች አንስቶ በሲዳማና በሐዋሳ ከተማ እስከ ቀበሌ መዋቅር ድረስ በተዘረጋዉ የዘረፋ; የስርቆት; የሙስና የአፈና ወዘተ ሰንሰለት ዉስጥ ያሉ ፀረ መንግስት ሁሉ እንደ መልማያቸዉ ተባረዉ  ቢቻል በሕግ እንድጠየቁ ማድረግ ካልተቻለ አባይን በማንኪያ እንዲሉ ይሆናል ነዉ የሕዝቡ መልስ:: ከተቻለ የተባለዉም ምናልባትም ሺፈራዉ የተባረረዉ እንደ ያረጋል አይሸሹም ልታሰር ነዉ; ሹመት የተባለዉም ለማዘናጋት ነዉ ለሚለዉ የሕዝብ ጉምጉምታ ሹፈራዉና ሰንሰለቱ ማን ማንን ያስራል ክልልም ፌዴራልም ያሉት እነማን እንደሆኑ እንተዋወቃለን:: በማለት አበክረዉ እየተከራከሩና በሕዝብ ዘንድ በሰፊዉ እያሰራጩ ስለሆነ ነዉ:;

6ኛ/  ሺፈራዉ ተባረረ በሱ ምትክ ማን ልመጣ ነዉ ለሚለዉ ጥያቄ እሱን ብቻ እንገላገል እንጂ ሰዉ ቀርቶ ዲያብሎስም ይሁን ነዉ የሕዝቡ ስምምነት በአጭሩ::

የተከበሩ አቶ ደሴ ዳልኬ

አሁን አሁን እንደተረጋገጠዉ በአዉሬዉ ምትክ የተባለዉ ዲያብሎስ ሳይሆን አንተ መተካትህን ሕዝቡ ሰማዉ : ሰምቶም ከአዉሬዉ አንፃር “ይሁን እስቲ እናየዋለን|” ብልም አብዛኛዉ ግን Indifferent ነዉ አመለካከቱ:: ምክንያቱም አንድና አንድ ብቻ ነዉ :: አንተን መርጦ የላከህ

ሃይል ያንንም አዉሬ አስቀምጦት የነበረ እንጂ ለሲዳማ ሕዝብ ካሉት ልጆቹ በችሎታዉና በንፁህ ሕሊና ይመራኛል የሚለዉን እንድመርጥ እድል ተሰጥቶት አንተ ብቸኛዉ የሲዳማ ሕዝብ ምርጫ ሆነህ አይደለም የመጣሂዉ :: አንተን ብቸኛ ምርጫዉ አድርጎ መርጦ ከላከህ አካል ዉስጥ አንዳንዶቹ ከኢህአደግና ከመንግስት ፖሊስ ዉጪ በሲዳማ ብሔር ላይ ምን አይነት የቁም ቅዠትና ጭፍን ጥላቻ ያላቸዉ እንዳሉ በሕዝቡ ይታወቃሉና:: ይህንን ቅዠቱን ያሳካልኛል በማለት እንደሆነ እሙን ነዉ :: አንተም እንደ ሺፈራዉ የሀ/ማርያምን አጀንዳ ለማሳካት ወንድምህን እህትህን እናት አባትህን እየጨፈጨፍክ በጎን ሆድህንና ኪስህን እየሞላህ በጭፍን እየተጓዝክ ከማይጋፉት የሕዝብ ተቃዉሞ ተራራ ጋር ትላተማለህ አትላተምም ያንተ ልቦና የሚያዉቀዉና በአጭር ቀናት ዉስጥ ራቁቱን ይፋ ሆኖ የሚታይ ጉድ ቢሆንም የአሁኑኑ ሳይሆን ያለፈዉን ማንነትህን በተወሰነ ደረጃም ቢሆን የሚያዉቁህ ከዲያብሎሱ ቁራጭ ከሺፈራዉ ጋር ልነፃፀርም የማይገባ መልካም አስተዳደግ ያለህ እንደ አዉሬዉና ተከታዮቹ መጽሐፍ ቅዱስ የሚትይዘዉና ቤተ ክርስቲያን የሚትሄዴዉ ዉስጣዊ ሰይጣናዊነት ተፈጥሮህን ለመሸፋፈን ሳይሆን በፈሪሀ እግዚአብሄረ የተሞላ ንፁህ ሕሊና የምታመልክ; እጅህ በንፁሃን ዜጎች ደምና እንግልት ያልተጨማለቀ; ከጉቦና ከሙስና የፀዳህ; ሥራህንና ሃላፍነትህን በችሎታና በእዉቀት የሚትወጣ ወዘተ ስለመሆንህ ይመሰክሩልሃል; እኔም ጭምር:: ልብ በል እያልኩ ያለሁት ከሶስት አመታት ወዲህ ስላለዉ ማንነትህ አይደለም:: ምክንያቱም ሆን ተብሎም ይሁን አላዉቅም ካንተ ሚኒስቴር መሆን አንስቶ በተለይም ከሱ መባረርና ባንተ መተካት ወዲህ ሺፈራዉና ሰንሰለቱ እኔም ሆንኩ ሌሎች ከሚናዉቀዉ ማንነትህ በተቃራኒ እያሰራጩት ያለዉ መርዘኛ ፕሮፖጋንዳ ጥርጣሬ ስለጫረብን ነዉና ሰዉ ነንና ለምን ተጠራጠ ራችሁ  እንደማትለን ነዉ:: ትንሽም ቢሆን ተጠራጠሩ ይል የለም ማጫፉ ቁልቁሉ?

አቶ ደሴ ዳልኬ ሁለት ፈተናዎች ይጠብቁሃል:: አንደኛዉና ዋናዉ የላከህ ቡድን የሚሰጥህን የመንግስትና የፓርቲ አጀንዳ ሳይሆን የተወሰኑ ባለሥልጣኖች የቡድንና የግል የሆነ አጀንዳ በድብቅና አንዳንዴም በይፋ የሚያራምዱት በየጊዜዉ የሚፈበርኩትና ሲነቃባቸዉ የሚያሽሹት የፀረ ሲዳማ ፖሊሲያቸዉን እንድታስፈጽም የሚያሳድሩብህ ጫና ሲሆን ሁለተኛዉ እንቅፋት ግን በአንተ ጥንካሬ; ብስለትና አቋም የሚለካ የአጭር ጊዜ ምናልባትም ረዥም ጊዜ ወስዶ እንደ ሺፈራዉ ከሕዝብ የሚያስወጣህ ከሺፈራዉና ከሰንሰለቱ የሚመጣብህ ጫና ሲሆን ካወክበት የነዚህ ጫና በሰከንድ ዉስጥ እንደ ጉም ተንኖ የሚጠፋ ነዉ :: በመሪያቸዉ ድንገተኛ መባረር የተደናገጡት የሰንሰለቱ አባላት ከመሪያቸዉ ጋር ሆነዉ ሁለት ስትራቴጂ ነድፈዉ እየጠበቁህ ነዉ:: ስላንተ ብቃትና ችሎታ ማነስ  በመሪያቸዉ ተሰብኮላቸዉ የልብ ልብ የተሰማቸዉ አባላቱ በተለያዩ ዘርፎች በአንተ ላይ ጫና በመፍጠር የነሱ ተባባሪ ሆነህ የሰንሰለቱንና የሺፈራዉን የሙስና; የግፍ የጭፍጨፋ; የከርሳምነት; የአመዝራነትና የትዳር ማፍረስ ለጋሲ

(Legacy) ለማስቀጠል ሌት ከቀን እያሴሩብህ ይገኛሉ:: እግዜር ያዉጣህ:: ቅን ከሆንክና በዱሮዉ ማንነትህ ያለህ ከሆነ የነሱ ዱለታና አዱማ ከንቱ ገለባ ነዉ :: እነሱ በሕዝብ ደም የተጨማለቀ ማንነታቸዉን ይዘዉ በቀይና አልጫ ፍሬሽ የተቀበተተዉን ከርሳቸዉን ዘርጥጠዉ መጥተዉ ልኮፈሱብህና ልፈትኑህ ቢሞክሩ ለቅንጣትም ያህል ቦታና ጊዜ ሳትሰጣቸዉ "ሂዱና ለማያዉቃችሁ ታጠኑ እናንተ ምናምንቴ ተራ ቀማኛዎች መንግስትን አሳሳች ሰይጣኖች ከፍቴ ጥፉ" በላቸዉ:: ወዲያዉም ይበተናሉና:: አይ እስካሁን በሕዝብ ደም ተጨማልቀዉ ራሳቸዉንና የቅርብ ዘመዶቻቸዉን ቢሊየነር ያደረጉና የሆኑትን መንግስት ምን አደረጋቸዉ? እኔም እስካሁን የተሞኘሁት ይበቃል ብለህ ተዘጋጅቶ ለሚጠብቅህ የጥፋት ቡድን ሰንሰለት ዉስጥ ለመቆራኘት ወስነህ መጥተህ ከሆነም መንገዱን ጨርቅ ያድርግልህ::

## ክፍል ሁለት : በሕዝብ አክ እንትፍ ተብሎ የተጠላበት የሺፈራዉንና የቡድኑ ማንነትና ምግባረ ብሉሹነት እንዴት ይገለጻል?

1ኛ/ የሲዳማን ሕገ መንግስዊ መብት ተፈታትነዋል:: ከሟቹ መለስ ዜናዊ ጀምሮ በሁሉም በይፋ ከሚታወቁት የሲዳማ ወዳጆችና ጠላቶች ጭምር ስለ ሕገመንግስታዊነቱ የተመሰከረለትን የሲዳማን የክልል መንግስትነት መዋቅር ዉሳኔዉን በመሃይም ጭንቅላታቸዉና በግርድፍ አፉቸዉ "ዉሳኔዉ ስህተት ነዉ ለሲዳማ ክልል አያስፈልገዉም ሲዳማ ክልል አልጠየቀም" በማለት በመህይምነት ድፍረታቸዉ ዘላብደዋል ቀባጥረዋል::

2ኛ የሲዳማን ብሔር ታሪክና ባህል አዛብተዋል አዳክመዋል:: ሲዳማ ከማንም በላይ ያል በረዘ ያልተከለሰና ለአለማችን የተረፈ የራሱ የሆነ የጀግንነት; የዲሞክራስ; የፍትሕ; የኢኮኖሚ; የባህል; የቋንቋ ወዘተ እሴቶችን የያዘ አኩሪ ታሪክ ያለዉ ብሔር ነዉ:: ይህንን አኩሪ ታሪክ ለማጥፋት ተልዕኮ ተሰጥቶት ሺፈራዉ ለአመታት ብዙ ብዙ ጥፋቶችን ሲያደርግ አሳልፎአል:: በተለይ በተለይ የተሰጠዉን ተልዕኮ ከማሳካት ባሻገር የዘረፋ ምኞቱንንም ጎን ለጎን ለማስኬድ ሲል የሲዳማን ታሪክ ለመጻፍ በሚል ሰበብ ስፍር ቁጥር የሌለዉን በጀት አስመድቦ ለተሰጠዉ የሲዳማን ታሪክና ባህል ማዛባትና ብሎም ማጥፋት ተልዕኮዉ የሚመቹትን አንዳንድ ምሁራን ተብዬዎቹን ከበጀቱ ሽርፍራፍ ቁራጭ እየጣለላቸዉና በተራ የአምባሳደርነት ሥልጣን በመደለል የሲዳማ ብሔር ታሪክ ሳይሆን የዴህዴንን ፕሮግራም አሳትሞ አሰራጨ:: ሕዝቡን ካበሳጬት ሆን ተብሎ ከተዛቡና ከተጣመሙ በመጽሐፍ ተብዬዉ ከተጠቀሱት በርካታ ጉዳዮች ዉስጥ ከ25 ሺህ በላይ ታጋዮች ተሰዉተዉ ከ1969 እስከ 1976 ባሉት አመታት ሁሉንም የሲዳማን ምድር ከደርግ ነፃ በማድረግ ለአሁኖቹ የሀገርቱ ገዥ ለሆኑት ለሕወሃትና ለኤርትራ መሪዎች ጭምር መጠለያ: ስንቅና ትጥቅ በመስጠት ትኩሱን የደርግን ወታደራዊ ሀይል

ተቋቁሞ ደርግን ያሸነፈ ሲአን (ሲዳማ አርነት ንቅናቀ) በኢትዮጵያ ብቸኛዉ የታጠቀና የተደራጀ የፖለቲካ ድርጅት መሆኑን አለም የመዘገበዉን ታሪክ ጥላሸት በመቀባት የሲዳማ ብሔር ታሪክ ነዉ ባሉት በዴህዴኑ ፕሮግራም መጽሐፋቸዉ “ሲአን በ1983 ነዉ የተመሰረተዉ” በማለት ዘላበዱ ቀጠፉ ዋሹ:: ለብሔሩ አርነት አንገታቸዉ ተቆርጦ በአደባባይ የተሰቀሉትንና በጦር ሜዳዉ ወድቀዉ የአዉሬ ሲሳይ የሆኑት የ25 ሺ ታጋዮችንና ተጋዳላዮችን ደም በታሪክ ዉስጥ ደመ ከልብ ሆኖ እንድቀርና የሲዳማ የጸረ ደርግ ትግሉና ጀግንነቱ ብሎም የከፈለዉ ወደር የለሽ መስዋዕትነት ታሪኩን ካዱና ዋጋ አሳጡ:: በዚህም ተልዕኮቸዉን ተወጡም; ተሸለሙም; ዘረፉም:: ከዚህ በተጨማርም በክልሉም ሆነ በፌዴራል መንግስትና ፖለቲካ ድርጅት ቲቪና ሬድዮ; ጋዜጣና መጽሔት; ሪፖርትና ቅስቀሳ ጽሑፎች ወዘተ የሲዳማን ብሔር የሚያዋርዱና የሚያጥላሉ በሬ ወለደ ልበወለድ እንጂ የብሔሩን ትክክለኛ ገጽታና መልካም እሴቶች እንዳይተላለፉና እንዳይጻፉ መመሪያ ተሰጠ:: በፌዴራሉና በተለይም በክልሉ ቲቪና ሬድዮ የሲዳማ ዘፈንና ጭፈራ ጥብቅ ትዕዛዝ በመስጠቱ እንዳይተላለፍ እገዳ ተጣለበት:: በኤፍም ሬድዮዉ የ56ቱ ብሔር ብሔረሰቦች ዘፈንና ጭፈራ ቀርቶ የአንድ ብሔር ዘፈንና ታሪክ እንድሰራጭ ትዕዛዝ በመተላለፉ አንዳንዴ የስቱድዮዉ ቴክኒሺያኖች ሰልችቶአቸዉ አንዱን ዘፈን ቢስ በማድረግ ትተዉት ነዉ መሰለኝ በተደጋጋሚ አንድ ዘፈን ለሰአታት ይደመጣል:: እንደዚሁም በትዕዛዝ ዘፈንና ጭፈራዉም ሆነ ከቲቪዉ ባክግራዉንድ እስከ ጋዜጠኛዉ አልባሳት የሌላ ብሔር ባህላዊ አልባሳት እንደሆነ አለም የሚያዉቀዉን እዉነታ በመቀማት የሌላ ብሔር ነዉ በማስባል በተገኘዉ አጋጣሚ ሁሉ ሁሉም እንድለብሰዉ ጥብቅ ትዕዛዝ በመስጠቱ ተለብሶ ይታያል:: ጉድ ለማየት ለተፈጠረዉ ለሀገሪቱ ሕዝብ ይሄዉ አልባሳት የሀገሪቱ ባንድራ ነዉ ተብሎ ሳይታወጅ ይቀራል? ቂቂቂቂ

**3ኛ የሲዳማ አመት መለወጫ ብሔራዊ በአል ፍቼ እንዳይከበር በአደባባይ ማወጁና በዩኔስኮ ተመዝግቦ በአለም ቅርስነት እንዳይመዘገብ ማስተጓጎሉ::**

የሲዳማ ብሔር በሀገሪቱ ካሉት 80 በላይ ብሔር ብሔረሰቦች ልዩ የሚያደርገዉ የራሱ የሆነ የሰአት; የቀናት; የወራትና የአመታት አቆጣጠር ያለዉ ብቸኛዉ ብሔር መሆኑ ነዉ:: ሲዳማ በአለማችን ካሉት 200 የሚሆኑ ሀገራት ዉስጥ የራሳቸዉ የሆነ የቀናት የወራትና አመታት አቆጣጠር ካላቸዉ ከ10 የሚያንሱ ሀገራት አንዱ ነዉ:: በሲዳማ የአዲሱ አመት የመጀመሪያ ቀን ፍቼ ተብሎ ይጠራል:: ቀኑም በከፍተኛ ድምቀት በዘፈን; በጭፈራና በቄጣላ ይከበራል:: እያንዳንዱ የሲዳማ ጎሳ ፍቼን የሚያከብረዉ በአቅራቢያ በሚገኘዉ በእያንዳንዱ ጎሳ የተቀደሰ የአምልኮና ሸንጎ ሥፍራ ጉዱማሌ ሲሆን የሲዳማ ብሔር በጋራ ደግሞ በብሔሩ ዋና ከተማ ሐዋሳ በሚገኘዉ ጉዱማሌ ነዉ:: በ1994 የነሺፈራዉ ቡድን የክልሉን ሥልጣን እንደተቆጣጠረ

የወሰደዉ የመጀመሪያዉ እርምጃ ሲዳማ የፍቼን በአል በሐዋሳ ጉዱማሌ እንዳያከብርና በሚሊዮኖች የሚቆጠር ሕዝብ ሐዋሳ መጥቶ ልያከብር ቀርቶ ጎመን ይዛ ከሚትመጣዉ አሮጊት አንስቶ ሲዳማ የሆነ ማንም ለገበያም ሆነ ለማንኛዉም ጉዳይ ሃዋሳ ከተማ እንዳይገባ እገዳ ጥለዉ ነበርና ለሚቀጥሉት 3 አመታት ሕዝቡ ብቸኛዉን ብሔራዊ በአሉን በሐዋሳ ከተማ ብቻ ሳይሆን በማንኛዉም ቦታ እንዳያከብር ጫና አደረጉ:: ከነዚህ አመታት በሃላ ብሔሩ የነሺፈራዉን ዱባ ጥጋብ ፋከራና አዋጅ ፋርሽ በማድረግ በአሉን በየአመቱ በከፍተኛ ድምቀት እያከበረ ቢያሳልፍም እነሺፈራዉ የበአሉን ድምቀት ለማደብዘዝ ዛቻና ማስፈራርያ አዋጅ ከማወጅ አልፈዉ በርካታ ቁጥር ያለዉን ጦር በማሰማራት ሕዝቡን ለማሸማቀቅ ቢጥሩም ሕዝቡ የሺፈራዉንና የካድሬዎቹን ድንፋታ ከመጤፍ ሳይቆጥር በአሉን አከብሮ ሲዉል ነበር:: በዚህ ብቸኛዉ ልዩና ደማቅ በሆነ የብሔሩ ብሔራዊ አዲስ አመት መለወጫ ፍቼ በአል ላይ የሲዳማ ተወላጅ በሙሉና ከብሔሩ ዉጭ የከተማዉ; የክልሉና የሀገሪቱ ሕዝቦችና የክልሉና የፌዴራሉ የመንግሥት አካላትና የሚዲያ ሰዎች በርካታ የዉጭ ሀገር ተመራማሪዎችና ቱሪስቶች ይሳተፉ ነበር:: የፌዴራሉ መንግስትም ለፍቼ በአል ድምቀት በየአመቱ በሂሊኮፕተር ቄጤማና አበባ እንዲሁም የመልካም ምኞት መግለጫ መልእክት የያዘ ወረቀት ይበትን ነበር:: በየአመቱ በበአሉ ላይ ሲሳተፉ የነበሩ የመንግስት አካላትና ጋዜጤኞች እንዲሁም የዉጭ ሀገር ቱሪስቶች በሀገሪቱ ብቸኛና ልዩ የሆነዉንና በከፍተኛ ሕዝብ ቁጥር በደማቅ የዘፈንና የጭፈራ ስልት የሚከበረዉን የፍቼን በአል በአለም ቅርስነት እንድመዘገብ እንቅስቃሴ ጀምረዉ ከሲዳማ ዞንና ከክልሉ ባህልና ቱርዝም መሥሪያ ቤቶች አስፈላጊዉ መረጃ እንድሰጣቸዉ ከፍተኛ ጥረት እያደረጉ ቢሆንም ጉዳዩ የሚመለከተዉ የክልሉና በተለይም የሲዳማ ዞን ባህል መምሪያ ሃላፍ በተሰጣቸዉ ትዕዛዝ መሰረት በአይነትም ሆነ በጥራት የተሟላ መረጃ ለጠያቂዎቹ በወቅቱ አሟልተዉ ሳይሰጡ ይሄዉና ከ8 በላይ አመታት ተቆጠሩ:: ከዚህም በተጨማርም የሲዳማ መንግስት ዋና ከተማ በሆነዉ በሐዋሳ ከተማ የሚገኘዉን የብሔሩን ቅዱስ የአምልኮና የሸንጎ ሥፍራ የሆነዉን ጉዱማሌ አቶ ሺፈራዉ በተሰጠዉ ተልዕኮ መሰረት ለአንድ ተራ ደላላ ነጋዴ ካልቸበቸብኩ የሚስቴን ቀሚስ ለብሼ ቁጭ ብዬ እሸናለሁ እያለ ሲፎክርና ሲያስፈራራ ሕዝቡ እጅግ ዘመናዊ የሆነ ሎጅ ለማስገንባት የመሰረት ድንጋይ የሚጣልበትን ቀን ቆርጦ ለተላላኪዉ የሚትለብሰዉንም ቀሚስ ይዘህ በዚህ ቀን በቦታዉ እንገናኝ በማለት መልዕክት ልኮበት በተባለዉ ቀን የመሰረት ድንጋይ ለመጣል ሲኬድ አጅሬዉ በቦታዉ ቀድሞ ደርሶ ቀሚሱንም ለብሶ የመሰረት ድንጋዩን እያመላለሰ እያለ ሕዝቡ ሲደርስበት የተሸከመዉን ድንጋይ ማጅራቱ ላይ አድርጎ ተደፍቶ "እገሌ ነዉ ያሳሳተኝና ይቅርታ አድርጉልኝ" በማለት ተንሰቅስቆ ሲያለቅስ ሽማግሌዎቹ አስጠንቅቀዉና መክረዉት ሲለቁት ግን ማን ነዉ ያዘዘህ ሲባል አጅሬዉ ጣቱን በወቅቱ የክልሉ ከፍተኛ ባለሥልጣን ወደነበረዉ ቀሰረ::

4ኛ/ ሲዳማን ከመንግስትና ከሌላዉ ሕዝብ ጋር ማጋጨት:: እሱና ግልገሎቹ የሚፈፅሙት ሙስና; ምግባረ ብልሹነትና አመንዝራነትን ለመሸፋፈን ብሔሩን የመንግስት ተቃዋሚና የሌላዉ ሰላማዊ ሕዝብ ጠላት አድርገዉ ማናቆር የእለት ተእለት ተግባራቸዉ ነዉ :: ለአብነት ያህል በምንም መመዘኛና በሁለቱ ብሔሮች የቆየ ታሪክ ዉስጥ የሌለ “የሲዳማ ለወላይታ ጠላትነት” አዋጅ በመንግስት ሚዲያ ማስነሰማቸዉ ይጠቀሳል:: እዚህ ላይ ሕዝቡ የታዘበዉ ሺፈራዉንና መሃይም ካድሬዎቹን ሳይሆን ባልተጨበጠ እዉነታ ላይ ይህ ሕዝብን ከሕዝብ የማጫረስ ጦርነት አዋጅን አጽድቀዉ ጦርነቱን ይፋ ባደረጉ የፌዴራል መንግስት ባለስልጣኖችን ነዉ :: አጅሬዉ በአጉል ብልጠቱ ከ1994 ጭፍጨፋ ጀምሮ እስካሁን ላለዉ ጅምላ ግድያ; እስራትና አፈና; ስድብና ዛቻ; ለምሁራኖቹ ከሥልጣንና ከሥራ መባረርና መታሰር; ለኢኮኖሚዉ ድቀትና ለቡናና ጫት ምርት ዋጋ መዉደቅና ለነጋዴዎች ኪሳራ ወዘተ እራሱን ንጹህ በማድረግ “እኔን አስገድደዉኝ ነዉ” በማለት በመያዣነት የሚያቀርባቸዉና ያለ ሥራቸዉና ያለሃጢያታቸዉ በመልካም ስማቸዉና ዝናቸዉ ላይ ጥላሸት እየቀባ የሲዳማ ብሔር በጠላትነት እንድያያቸዉ በማድረግ ለአመታት በብሔሩና በአንዳንድ የክልልና የፌዴራል መንግስትና የፖለቲካ ድርጅት ባለስልጣኖች ላይ ማለትም ከክልሉ አለማየሁን ከፌዴራል ደግሞ በሕይወት በነበሩ ጊዜ መለስ ዜናዊን; ሬድዋን ሁሴንን; መኩሪያ ሃይሌን; በተለይ በተለይ ደግሞ ሀይሌ ማርያምንና በረከት ስምኦንን በሕዝቡ ዘንድ እንድጠሉ ከፍተኛ የሀሰት ፕሮፖጋንዳ በሰንሰለቱ አማካይነት ያሰራጭ ነበር:: ያኔ ለሥልጣንና ለጥቅም ሲያሸረግዱለት ከነበሩት ካድሬዎችና ደላላ ነጋዴዎች ጭምር በሱ መባረር ሕዝቡ ከዳር እስከ ዳር ተደስቶ በየፈርጁ ደስታዉን እየገለጸና ምስጋናዉን እያቀረበ ነዉ የሚል መርዶ በየአቅጣጫዉ ካሰማራቸዉ ወሬ ለቃቃሚዎቹ ሰምቶ በመበሳጨት ከተባረረበት እለት ጀምሮም በሰንሰለቱ አማካይነት በባለስልጣኖቹና በሱ ቦታ በተመደበዉ ፕሬዝዳንት ላይ በሕዝብ ዘንድ ጥላቻና ጥርጣሬ በሚጭር መልኩ ሲዳማ ለአሁኑ በኔ መባረር ተደስቶ ይሆናል ትንሽም ሳይቆይ “በገመድ ታስራ የሚትኖረዋን ላም አማርሬ ሸጬያት በምትኩዋ ብረት የምትቆረጥመዋን አመጣሁ የምልበት ቀን ይመጣል” እያለ በጀት መድቦ በሰፊዉ እየሰራ ነዉ::

5ኛ የብሔሩን ሕልዉና የሚፈታተኑ ኢ-ሕገመንግስታዊ የሆኑ ትንኮሳዎችን መንዛት:: ከዴህዴን ቢሮ ይሁን ወይም ከነ አቶ አለማየሁና ከአቶ ሺፈራዉ የግል ኮምፕዉተር አይታወቅም በየጊዜዉ የሲዳማን ብሔር ትዕግስት የሚፈታተኑ መሰረት የለሽና ኢ-ሕገመንግስታዊ የሆኑ ሰነዶች ለዉይይት ቀረቡ ይባላል:: ሕዝቡ በነዚህ ትንኮሳዎች ስሜት ዉስጥ ይገባና ትርምስ ይፈጠራል::ካድሬዉና ሰራተኛዉ በነዚህ ሰነዶች ላይ በመወያየትና በማወያየት አብዛኛዉን የልማት ሥራ የሚሰሩበትን ጊዜ የራሳቸዉንም ሆነ የአርሶ አደሩን

ሥራ ሲያስፈቱ ይከርማሉ; ከርመዋልም:: ተማሪዉም ከትምህርቱ ይስተጓጎላል:: ለአብነት ያህል በ2004 ከዴህዴን ቢሮ ለዉይይት ቀረበ የተባለዉ ለራሳቸዉም ቢሆን ትርጉሙን በዉል የማያዉቁትን የ"ሜትሮፖልትያን" ሰነድ በማለት የተሰራጨና በዚህም ሳቢያ በሲዳማ ክልል የተፈጠረዉ ሁከትና ትርምስ ይታወሳል:: ግርግር ለሌባ ይመቻልና አጅሬዉ ሺፈራዉ በዚህ ሰበብ ማስትሬቶችን ብቻ እያስለቀመ ከ112 በላይ የሚሆኑትን ምሁራን አሳፈሰ; አሳሰረ:: ግማሾቹ ሀገር ለቀዉለት ኮበለሉ:: ይህ ኢ-ሕገመንግስታዊ ሰነድ አጠቃላይ የሲዳማን ብሔር ከዳር እስከ ዳር አስቆጣ:: ሥራ ቆመ:: ትምህርት ቆመ:: እርሻ ቆመ:: የሕዝቡ ቁጣ ከጫፍ እስከ ጫፍ ምድርቱን ሲያናዉጥ አጅሬዉ አቶ ሺፈራዉ "ይህ ሰነድ የተባለዉ የሌለ ሕጋዊ አይደለም እኔ በሌለሁበት የተሰራጨ ሰነድ ነዉ ያልተነጋገርንበትንና ያልፀደቀ ሰነድ በማዘጋጀትና በማሰራጨት ሁከት የፈጠሩት ባለሥልጣኖች ይጠየቁበታል" በማለት ዴህዴንና ባለሥልጣኖቹን ኮንኖ እሱ ግን የሕዝብ ወዳጅ የሆነ መሰለዉ:: ሰነድ ነዉ ተብዬዉን ሺፈራዉ ራሱ ለዉይይት አቅርቡ በማለት ወደ ዉጪ እንደሄደና ካለበትም ሀገር ሆኖ በየደቂቃዉ ለካድሬዎቹ መመሪያና ትዕዛዝ እየሰጠ ሂደቱን ይከታተል እንደነበር ይታወቃል:: ያ ሁሉ ሰዉ ከሹመትና ከሥራ ከተባረረ; ከታሰረና ከታጎረና ቢያንስ ለሦሥት ወራት በክልሉ የመንግስትና የሕዝብ ሥራ ተስተጓጉሎ "ሰነዱ ከመንግስት የቀረበ አይደለም|" ማለት የምን ድራማ ነዉ? ሰነዱ ከድርጅትና ከመንግስት ቢሮ ካልወጣ ሰነዱን ይዘዉ ቢያንስ ለ2 ወራት በተለያዩ የካድሬና የመንግስት ሰራተኞች መድረክ ሲያወያዩ የነበሩና በዚህ ሐሰተኛና ኢ-ሕገ መንግስታዊ የሕዝቡን ሕልዉና የሚፈታተንና የሚያዋርድ ሰነድ በማሰራጨት ለዚያ ሁሉ ሁከት ብጥብጥ ሥራ መፍታት እስራትና እንግልት መንስኤ የሆኑ ባለሥልጣኖች ላይ ምን እርምጃ ተወሰደ? ሌላዉ ለአብነት የሚጠቀሰዉ ካለፉት 3 ወራት ወዲህ እየተናፈሰ ያለዉ ዉዥንብር "የሐዋሳ ከተማ ለፌዴራል ተሰጠች; የሲዳማ ክልላዊ መንግስት መናገሻ ከተማ ከሐዋሳ ዉጪ ልሆን ነዉ የከተማዋ አስተዳደር በስብጥር ልሆን ነዉ ወዘተ" በማለት የሕዝቡን ስሜት በመፈታተን ላይ ናቸዉ:: እንደዚህ አይነት ዉዥንብሮች ለአመታት እየተነዙ የቆዩ ቢሆንም በሕዝቡ ቁጣ እየተመለሱ ቆይተዋል:: እንደዚህ አይነት ኢ-ሕገ መንግስታዊ ሰነዶችና ዉዥንብሮች አሁንም ሆነ ወደፊት በሲዳማ ሕዝብ ዘንድ ቦታ አይኖራቸዉም:: እነዚህ ዉዥንብሮች በሲዳማ ምድር ተግባራዊ የሚሆኑት እናት ማህፀን ዉስጥ ካለዉ ጽንስ ጀምሮ 6,7ቱም ሚልዮን ሕዝብ በጅምላ ጨራሽ ኬሚካል መሳሪያ ዶግ አመድ ሲደረግ ብቻ ነዉ:: ለካ ይህ ብቻም በቂ አይሆንም::ለካስ ከ 1 ሚልዮን በላይ የሲዳማ ብሔር ተወላጅ በሀገር ዉስጥና ዉጭ በሁሉም የአለም ሀገራት ተሰራጭተዉ ነዉ ያሉት? ምን አይነት የማይመች አስቸጋር ሕዝብና የቁም ቅዠት ነዉ ጃል?

6ኛ የሲዳማን ዳር ድንበር መሬት ያለ ሕግ አግባብ ለሌላዉ አሳልፎ መስጠታቸዉ:: ለአብነት ያህል በወላይታ; በወንዶ ገነት; በሀርበጎና; በሼሎ; በቦሬና ወዘተ ያለዉን ከጥንት ጀምሮ ሲገብር ሲያለማና ሲቀበርበት የኖረዉን የሲዳማን መሬት በማን አለብ ነት ለገንዘብና ለሥልጣናቸዉ ሲሉ ሸጠዋል; ቸብችበዋል::

7ኛ የሲዳማን ብሔር ብኩርና ሸጠዋል:: ሲዳማ ባለዉ የሕዝብ ብዛትና ለሀገሪቱ ከሚያበረክተዉ የኢኮኖሚ ድርሻ; ካለፈዉ ትግሉና ካለዉ የተማረ ሰዉ ሃይል አንፃር ከኦሮሚያና ከአማራ ብሔር ቀጥሎ በፌዴራል; በአዲስ አበባና በክልሉ ማግኘት የሚገባዉን ቁልፍ የሥልጣንና የበጀት ድርሻ አሳጥተዉታል:: ከክልሉ አልፎ በሀገር ደረጃ የሚኖረዉን ሃያልነቱንና በኩርነቱን አሳልፎ ለሌላ ሰጥተዋል::

8ኛ የሲዳማን ልማት አደናቅፈዋል ሺፈራዉ በራሱ ባመጣዉ እኩይ ተፈጥሮዉና ፀረ ሕዝብ ድርጊቱ የሲዳማ ሕዝብ አንቅሮ ስለተፋዉ ያንን ለመበቀል በፌዴራልና በክልል የሚከናወኑ ማንኛዉም ፕሮጀክቶች በሲዳማ ዉስጥ እንዳይሰራ "ሲዳማን አይርሽ አዉሮፓ አድርጎታልና ምንም አያስፈልገዉም" በማለት እየተከላከሉ ላለፉት 22 አመታት በሲዳማ ክልል ዉስጥ አንዳች የረባ ልማት እንዳይሰራ አድርገዋል:: "ሲዳማ ለም ነዉ ጥጋብ ነዉ" እያለ የተራበዉ በሚሊዮኖች የሚቆጠር ሲዳማ በረሃብ አለንጋ እንድገርፍ ምክንያት ሆነዋል::

9ኛ ሲዳማን በጎሳ; በወረዳና በቤተሰብ መከፋፈሉ ሺፈራዉ ያወቀ መስሎት ራሱን አንዴ የዚህ ወረዳ ወይም ጎሳ ሌላ ጊዜ የዚያ ወረዳ ወይም ጎሳ ነኝ እያለ አንድ ጊዜ ለአንዱ ወረዳ ሌላ ጊዜ ለሌላዉ ወረዳ የወገነ እያስመሰለ የሲዳማን ብሔር አንዱን ጎሳ ከሌላዉ ጋር አቃረነ; አጋጨ አከፋፈለ:: ራሱ በፈጠረዉ የማንነት ቀዉስ ተዘፍቆ የማንም ሳይሆን ባዶ ሜዳ ላይ ሲቀር በአጠቃላይ በሲዳማ ብሔር ላይ ጥላቻ አደረበት; ተበቀለም:: ከሥሩ የመለመላቸዉም ጥቃቅኖች ከላይ እስከ ቀበሌ ያለዉን መዋቅር በተመሳሳይ ጎሳዊ ፖለቲካ ሞሉትና አንዱን ጎሳ በሌላዉ ላይ በጠላትነት አስነሱ:: በሲዳማ ዉስጥ ታይቶና ተሰምቶም በማይታወቅ ሁኔታ ካድሬዎቹ እገሌ የዚህ ጎሳ ወይም የዚያ ቤተሰብ ነዉ በማለት ሹመት ሥራና ፍትህ በደምና በጥቅም ለተሳሰሩ የሰንሰለቱ አባላትና ቤተሰብ ብቻ በማከፋፈል ሌላዉን ሕዝቡን ባዕድ አደረገት:: ሕዝቡም በሺፈራዉና በሰንሰለቱ ካድሬዎች ድርጊት እጅግ ተማረረ:: መንግስትንንም እንድርቅ አደረጉት::

10ኛ በሲዳማ ደም መጨማለቁ በግንቦት 16/1994 በሎቄና ሎካ አባያ በ1998 ከጥር እስከ ሰኔ ባሉት ወራት በመቶዎች የሚቆጠሩ ንፁሃን ዜጎች የተጨፈጨፉበትን ታሪክ ያስታዉሱ:: የሰንሰለቱም አባላት በጥቆማ ሐሰተኛ ወሬ በማመላለስና በምስክርነት ተሳትፈዋል::

11ኛ ጅምላ እስራትና አፈና  በ1994 (ከ2500 በላይ) ምሁራንና ታዋቂ ሰዎች; ሽማግሌዎችን ነጋዴዎች; ተማሪዎችንና ወዘተ ; በ1998 (4550) የሚደርሱ ወጣት ተማሪዎችና ምሁራን; በ2001 (ከ120 በላይ) ምሁራንን;  በ2003ና በ2004 (150 የሚደርሱ) የመጀመሪያና ማስትሬት ዲግሪ ያላቸዉን ብቻ መርጦ; በ2005 (210) ማስትሬት ዲግሪ ያላቸዉን ምሁራን ብቻ በመምረጥ ወዘተ በተለያዩ ጊዜያት በሺፈራዉ ቀጥታ ትዕዛዝ በተፈበረከ ሐሰት ወንጀል በሰንሰለቱ አባላት ጥቆማና መስካርነት ከሹመትና ከሥራ ተባረዉ ታሰሩ ታጎሩ::

12ኛ ታዋቂ ምሁራንን ማሳደድ  የሺፈራዉ ትልቁ ሰይጣናዊ ተፈጥሮዉ ታላላቅ አስተሳሰብና ራዕይ ያላቸዉን ምሁራንን የጎሳ መሪዎችን ባለሀብቶችንና የመንደር ሽማግሌ ሳይቀር ይመቀኛል ያሳድዳል ለማጥፋት ሳይተኛ ያድራል:: Superior Minds always feared by Inferior Minds የሚሉት ሐቅ በሱ እዉነት ሆነና በራሱ የትምህርት ደረጃና ጥራት በችሎታዉ በእዉቀቱና ራሱ በፈጠረዉ የማንነት ቀዉስና የሚመ ዉን ታዋቂነትና ሕዝቡ ስለነፈገዉ በከፍተኛ የበታችነት ድጥ ዉስጥ የተዘፈቀዉ ሺፈራዉ በሄደበት ሁሉ ዝናቸዉና ክብራቸዉ የሚነገርላቸዉን ምሁራን በምቀ ነት መንፈስ ተሞልቶ ፈራቸዉ::  የነዚህን ታዋቂ ምሁራንንና የሀገር ሽማግሌና ባለ ሀብቶችን መልካም ስምና ዝና ለማጉደፍ ለጥቃቅን ወሬ ለቃሚና አሰራጭ ሰዎቹ ሚሊዮን ብሮችን በጀት እየመደበ በሕዝብ ዘንድ በመልካም አርአያነታቸዉ በትምህርታቸዉና በሥራ ብቃትና ችሎታቸዉ ከሲዳማ አልፎ በክልልና በፌዴራል መንግስት ደረጃ የተመሰከረላቸዉን የሲዳማ ሕዝብ አለኝታ መመኪያና መከታ የሆኑትን የሲዳማ ምሁራንን በራሱ ተነሳስቶና የሌሎችን አጀንዳ ለማሳካት ብሎ ካሉበት ሥልጣንና ሥራ በሐሰት የመንግስት ጠላትነት እያስፈረጀ እንድባረሩ አደረገ:: እነዚህ ታዋቂ ምሁራን ከሀገር ዉስጥና ከታወቁ የአዉሮፓና የአሜሪካ ዩኒቬርስቲዎች ተፈላጊ በሆኑ የትምህርት ዘርፎች ሁለተኛና ሦሥተኛ ዲግሪ ያላቸዉ ስለሆኑ በችሎታቸዉ የትም ተወዳዳሪ ሆነዉ መቀጠር ይችላሉና ሲዳማን ለቀዉ ሀገር ዉስጥና በዉጭ ሀገራት በተለያዩ መንግስታዊና መንግስታዊ ባልሆኑ አለም አቀፍ ድርጅቶች ተቀጠሩ :: ሲዳማ በማንኛዉም መድረክ በእዉቀታቸዉና በችሎታቸዉ ተማምነዉ የሚከራከሩለትን መመኪያ ልጆቹን ቡዳዉ ሺፈራዉ በየአመቱ ቅርጥፍ አድርጎ ሲበላቸዉ የሕዝቡ ልብ ከነዚህ መኩሪያዉና መመኪያዉ ከሆኑት ልጆቹ ጋር ከሀገር ሀገር አብሮአቸዉ ተጓዘ:: የገዛ ወንድሙን ሥጋ የሚበላዉን ሺፈራዉንና አባላቱን ጭራቆች ናችሁ ብሎ ከየጎሳቸዉ ማህበራዊ ስርአት አገለላቸዉ :: በነዚህ ታላላቅ አለም አቀፍ ምሁራን ምትክ ምንም ልምድና ችሎታ የሌላቸዉን ገና ለመጀመሪያ ዲግሪ አልፋ ኮሌጅ የርቀት ትምህርት እየተከታተሉ ያሉትን “ሲዳማ ያለዉ የተማረ ሰዉ ይህ ብቻ ነዉ” በማለት ለሚኒስርነት ካጨዉ ሚዜዉ ጀምሮ በክልል በዞን በሐዋሳ ከተማ በየወረዳዎቹ እስከ ቀበሌዎቹ መዋቅር

ድረስ ከትምህርት ትምህርት ከልምድ በቂ ልምድ ከአመራር ችሎታ ምንም አቅም ከወገናዊነት ከቅንነትም ወዘተ የሚነገርላቸዉ የሌላቸዉን እንደራሱ በማንነት ቀዉስና በበታችነት ጭቃ ዉስጥ የሚዳክሩትን ትናንሾችን በሲዳማ ኮታ በፌዴራል በክልልና በዞን በሐዋሳ ከተማ በሹመትና በሥልጣን ላይ ሲያስቀምጥ አብዛኛዎቹ ለቦታዉ ብቁ ሳይሆኑ ሲቀሩ “ምነዉ ሲዳማ ሰዉ የለዉም እንዴ” አስባሉ :: እነዚህ ማፈሪያዎችም በሚያሳዩት ሽልፋነትና ልፍስፍስነት በሌላዉ ዘንድ የብሔሩን ገጽታ አበለሹ:: እነዚህ ሺልፋ ካድሬዎች እንካን በሲዳማ ብሔር ላይ የሚነሳዉን አግባብነት የሌለዉን ትንኮሳና ድፍረት በመድረክ ሕጋዊ ሳይንሳዊና ሎጂካል በሆነ ሁኔታ ተከራክረዉ ማሳመን ቀርቶ ሲዳማ ለመሆናቸዉ ሲደበቁ ብዙዎቹ በብዙ መድረክ ታይተዋል:: በአንድ በኩል ሲታይም አይፈረድባቸዉም ችሎታዉ ብቃቱና ወገናዊነቱ የላቸዉማ:: የነሱ ችሎታ አርሶ አደር ላይ ሄደዉ መዘላበድ ነዉ :: አፋቸዉ የሚከፈተዉ መሸታ ቤትና ለሐሜት ነዉ :: የሺፈራዉም ተልዕኮ ይህ ነበርና ይደሰታል:; ግን የሲዳማ ምሁራን ችሎታ የአመራር ብቃት በራስ መተማመን ከማንም በላይ ሀ/ማሪያም ያዉቀዋል:: አሁን ከላይ እስከ ታች ሲዳማን ይወክላሉ ተብለዉ በትንሹ ሺፈራዉ በራሱ ልክ የሰፋቸዉ ትናንሾቹ ካድሬዎች ሲዳማ ዉስጥ ምንም ተሰሚነትም ተቀባይነትም የሌላቸዉ እንካን ሌላዉ የገዛ አባታቸዉም እዉቅና የማይሰጣቸዉ መሆናቸዉን ሳያዉቁ ሁሉም ሲዳማ እንደነዚህ ሺልፋ ካድሬዎች መስሎአቸዉ እነ አለማየሁ አሰፋ ሲዳማ ዉስጥ ሮጠዉ ሲገቡ ወደ ዋናዎቹ ጉምቱ ምሁራን ሳይደርሱ በትንታግ 2ኛ ደረጃ ተማሪዎች ብቻ በወላፈን ተለብልበዉ መመለሳቸዉን ያስታዉሱታል:: በአሁኑ ጊዜ በፌዴራልም ሆነ በክልሉ የመንግስት መዋቅር አንድም የሲዳማ ብሔር ተወካይ እንደሌለ መታወቅ ያለበት ሲሆን  ዞንና ከተማ አስተዳደር በተባለዉም መዋቅር ዉስጥ አንድም ሕዝቡ እኔን ይወክለኛል በማለት እምነት የሰጠዉ ካድሬና ሹመኛ እንደሌለ መታወቅ አለበት:: በአሁኑ ጊዜ በየእርከኑ ያሉ ምሁራን ተብዬዎች መንግስትንና ሕዝብን አጋጭተዉና ብጥብጥ ቀስቅሰዉ በዚህ ብጥብጥ ወቅት በሚስቶቻቸዉ ወይም በዉሽሞቻቸዉ ድርያ ዉስጥ ተሸሽግዉ ያልሆነ መረጃ ለሺፈራዉና ለሌሎች እየደወሉ የባሰ ሁከት የሚፈጥሩ ከሁከቱም በሃላ ከሺፈራዉና ከሌላዉ ሽልማት የሚቀበሉ ናቸዉ::

13ኛ የሲዳማን ባለሀብቶችና ነጋዴዎችን እንድከስሩ ደባ ሰርቷል::  በአብዛኛዉ በቡናና በጫት ንግድ የተሰማሩትን የሲዳማ ነጋዴዎች ሆን ተብሎ ለተወሰኑ ግለሰቦችና ቡድኖች እንድመች ተደርጎ በተዘረጋዉ የቡናና የጫት ግብይት ስርአት ተጠቃሚ እንዳይሆኑና ከንግዱ አለም ገበያ ተወዳዳሪ እንዳሆኑ ተደርጎ አብዛኛዉ የሲዳማ የጫትና ቡና አምራች አርሶ አደሩና ነጋዴም ለኪሳራ እንድዳረግ ሲፈረድበት እሱና ቡድኑ ግን በተዘዋዋር ቅብብሎሽ ኪሳቸዉን ሲሞሉ ከርመዋል::

14ኛ በሙስናና በጉቦ የተዘፈቀ ነዉ:: ሺፈራዉ ሌት ከቀን የሚያስበዉና የሚያሳካዉ የመንግስትንና የፓርቲዉን ተልዕኮ ሳይሆን ከሐዋሳ ከተማ ቦታ ሺያጭ ከኬላ ከፍትህ አካላት ከባለሀብቶች ከአርሶአደሮች ከጫትና ቡና ነጋዴዎችና ደላላዎች ከመንግስት እቃ ግዥና ኮንስትራክሽን በጀት በሰንሰለቱ አማካይነት በአይነትና በጥሬ ገንዘብ የሚገባለትን ገንዘብ መጠ ን ነዉ :: እዉነቱን ለመናገር ሙስናና ጉቦ በአደባባይ የሚቀባበልበት እንደ ደቡብ ክልል የለም ማለት ይቻላል:: በደቡብ ገንዘብ ያለዉ የፈለገዉን ያሾማል ያሽራል ያሳስራል ያስፈታል ልገድልም ልያስገድልም ይችላል:: የክልሉ ፕሬዝዳንትነትና ጳ ነት በባለ ሀብቱ እጅ ነዉ:: ሺፈራዉ በአሁኑ ጊዜ ያለ ማጋነን ከሀገሪቱ አልፎ በአለም ደረጃ በቢሊዮነሮች ተርታ የሚያሰልፈዉን ሀብትና ንብረት አከማችቶአል አሸሽቶአል:: የሰንሰለቱ አባላትም እንደየ ታማ ነት ደረጃቸዉ ሚሊየነሮች ሆነዋል:: እነሱ ሚሊየነሮች በሆኑ ቁጥር ከ6.7 ሚሊዮን ሲዳማ በሺፈራዉ ዘመን ከ3 ሚሊዮን በላይ ሕዝብ በከፋ ረሀብ በማለቅ ላይ ናቸዉ:: ማስረጃዉን በሲዳማ ታሪክ የሌለ ለማ ነት ኅዳና ተዳዳርነት ሥራ አጥነት ተንሰራፍቶ በሐዋሳ ከተማ ብቻ ከ25,000 የሚበልጡ ሕፃናትና አቅመ ደካማ አሮጊቶች ለልመና ተሰማርተዋል:: ዱሮ በልመናና በኅዳና ተዳዳርነት የሚታወቁት በመሪዎቻቸዉ አመራርነት በሲዳማ ሀብት ከጥቃቅን ንግድ እስከ ባለሀብትነት ድረስ ሁኔታዎች እየተመቻቹላቸዉ ሲሄዱ የሲዳማ ልጆች ግን መሪ በማጣታቸዉ በገዛ ሀብታቸዉ በገዛ ቀዬአቸዉ ለማኝ ሆነዉ እያዩ ማፈሪያዎቹ ሺፈራዉና ሺልፋ ካድሬዎቹ ግን ልማታዊ መንግስት ሕዝቡን ምርት በምርት ሀብት በሀብት እንዳደረገ በድፍረት ሲናገሩ ትንሽ እንካን አያፍሩም :: አዎ ሕዝብ ማለት ሺፈራዉና በጣት የሚቆጠሩት የሰንሰለቱ አባላት ከሆኑ ልክ ናቸዉ እነሱማ ምን ገዶአቸዉ::

15ኛ አመንዝራነቱ አቶ ደሴ እርስዎም ሆኑ ሁሉም የኢህአደግና የመንግስት ባለስልጣናት ዘንድ ከሚታወቀዉ በቅርቡ ከተከሰተዉ የአቶ ሺፈራዉ ከአንድ የክልሉን ከፍተኛ የሕዝብ አደራ ያለበትን መ /ቤት ከሚትመራዉ ባለሥልጣን እስከ ልጅ መዉለድ ቅሌት አንስቶ በቢሮ ካሉ የበታች ሴት ሰራተኞች ቡና ቤት ሽርሙጣዎች ከባለ ትዳሮች ከአዛዉንቶች ከተማሪዎች ጋር የማገጠበት የባለገበት ሥልጣንና የከተማ ቦታ የሰጣቸዉ ዉሽሞቹ ስንቱ ይቆጠራል? የስንቱ ትዳር ፈረሰ ክብሩን ሳይጠብቅ በየቦታዉ ለኩታራዎችና ለዱርየዎች ሱሪዉን እያወለቀ ለስንቱ ድቃላ ቀለብ እየሰፈረ እየኖረ ነዉ:: የሱ አመንዝራነት በየመድረኩ ሲዘረዘር የብሔሩም ስም መነሳቱ ይቀራል ተዋርዶ አዋረደዉ እንጂ ሕዝቡን:: ምን እሱ ብቻ! ተከተል አለቃህን ነዉና ሕጉ ከክልል እስከ ቀበሌ በችሎታቸዉ ሳይሆን በዝምድና የተሰገሰጉት ግልገሎቹ ሁሉ በማን አለብኝነት የዘረፉት ገንዘብ እየረጩ ሴት የተባለዉን ሁሉ ተማሪ ባለትዳር ሴትኛ አዳሪ የቤት ልጅ አቅመ ሔዋን ያልደረሱና አዛዉንት ሳይቀር ከሁሉም ጋር አመነዘሩ ሴሰኑ ባለጉ

አባለጉ:: በሐዋሳ በአንድ ቀን አዳር ብቻ ሺዎች ብርን የመዛቁና እድል የቀናቸው ደግሞ የከተማ ቦታ ፐላን ሥራና ሥልጣን የመታደል ዜና የሰማ ሴት ሁሉ ወደ ሐዋሳ ጎረፈ:: የከተማው ቤት ሁሉ የዳንስ የጭፈራ የሺሻ የጫት ቤት ሆነ:: የአንደኛ ደረጃ ሕፃን እስከ ዩኒቬርስቲ ያሉ ተማሪዎች ባለትዳሩ ሳይቀር ወደነዚህ ቤቶች ጎረፈ:: ከተማው በአለም ከታወቁ የሴክስ እንዱስትሪ ከተማዎች ተርታ ተሰለፈ:: ተራዉም ሰው የባለሥልጣኖቹን ፈለግ እየተከተለ በየቦታው በየሜዳው በየመንገዱ እንስሳ ሆነ:: ከተማዋ ከሁሉም ሀገሪቱ ክፍል እየመጡ የሚከማቹበት የዱርዬዎች የነፍሰ ገዳዮች መናሃሪያ ሆነች መንገዱ መንደሩ ሰፈሩ ሁሉ በዋይታ በጫጫታ በእሪታ ወዘተ ተጥለቀለቀ:: ማን ይቆጣጠረው? ሐዋሳ የመጽሐፍ ቅዱስዋ ሰዶም ገሞራ ሆነች::

16ኛ በጠንቋይና ፈልፈላ ያምናል ይመራምል ::እሱም በራሱ ጠንቋይና ፈልፈላ ነው :: ሺፈራው በአደባባይ ፕሮቴስታንት እምነት ተከታይ እንደሆነ ያስመስላል:: እየቀያየረም ቤተ ክርስቲያን ሲሄድ ይታያል:: በዘረፈው ገንዘብ በቤቱ ኮንፈራንስ አዘጋጅቶ ያበላል:: ምጽዋት አሥራት ስጦታም ይሰጣል:: በእግዚአብሔር ቤትም በተሰገሰጉ ሰባኪና ነቢያት ነን በሚሉና ያለምዕምናን ምርጫ በሱ ጫና በቤተ ክርስቲያን መሪነት የተቀመጡ በነሱ የተነሳ ምዕመናን እምነታቸዉንና ቤተክርስቲያኖችን እየለቀቁ እንድጠፉና የሃይማኖትና የጎሳ ክፍልፍል በማስፋፋት የሃይማኖት ግጭትና ጥላቻ እንድስፋፋ እያደረጉ ባሉ የሰንሰለቱ የጥፋት ቡድን አባላት አማካይነት ስለሱ ጽድቅ ይነዛል:: እነዚህ ሐሰተኞች በፖለቲካና በመንግስት መዋቅርም ጣልቃ በመግባት የፈለጉትን ያሾማሉ ያስባርራሉ:: በሐሰት ወንጅለው መስክረው ያሳስራሉ:: የሺፈራው ሌላዉና ዋናው ገጽታው ግን ጠንቋይነትና ፈልፈላነት ነው ::በዚህ በተካኑ ሽማግሌዎች አማካይነት መቼ የት በማን ላይ ምን ማድረግ እንዳለበት ያስጠነቁላል ይፈጽማልም:: ለዚህም ማስረጃው ሰው ሁሉ እንደራሱ እየመሰለው ግለሰብንም ሆነ ሕዝብ በጅምላ ለትንሹም ሆነ ለትልቁም ጉዳይ “Gojaamo” ፈልፈላ “Gojaamma” ፈልፈላዎች የሚል ስድብ ብቻ ነው ከአፉ የሚወጣው::

17ኛ ፈሪ ነው ተፈጥሮው ይሁን ወይም በየጊዜው በሕዝብ ላይ የሚፈፅመው ወንጀል እረፍት እየነሳው ይሁን አይታወቅም ሺፈራው በጣም ፈሪ ነው:: ፈሪ ሰው መሪ ልሆን አይገባዉምና በፈሪነቱ እየበረገገ ስንቱን ፈጀ::

18ኛ ከርሳም ሆዳም ነው ሺፈራው ሆድ አምላኩ ነው:: ለሺፈራው ሆዱን የሞላለት ሰው የፈለገውን ያገኛል:: ሲቆርስም ሲጎርስም ያየ ከአጠገቡ ይሸሻል:: የአቆራረስና የአጎራረስ መጠኑ ይዘቱ ስግብግብነቱ ያው ያኔ ወረዳ ላይ ከነበረው የተለወጠ ነገር የለዉም:: የያኔው አልጠግብ

ባይነቱ አሁንም አልለቀቀዉም :: ምግብ እያሳየዉ ማንም ገደል ይዞት ልገባ ይችላል:: ምግብ አይመርጥም ቦታ አይመርጥም:: በሲዳማ ብሔር ለመሪነት ከሚያበቁት መስፈርቶች አንዱና ዋነኛዉ ወንድ ልጅ ለሆዱ ያለዉ ቁጡብነት ነዉ :: ያገኘዉን ማግበስበስ የለበትም:: ሲቆርስም ሲጎርስም በልኩና በሥርአት መሆን አለበት:: እየራበዉም ጠግቤያለሁ ብሎ ማሳለፍ አለበት:: ሲዳማ ሲመርቅ ኮኬ ኤማሮሄ ማለቱ ከባድ አባባል ነዉ :: ሆዳም ምኑ ይታመናል? ዔሳዉ ለሆዱ ብሎ አይደለም ብኩርናዉን አሳልፎ የሸጠዉ:: የኛዉ ሺፈራዉ ቢሆንስ የዚያን ጊዜ ለታየዉ ለሆዱ መሙላት ተስገብግቦ አይደለም የራሱን ብኩርና አሳልፎ የሰጠዉ:: አሁንም ኮኬ ኤማሮ !!! አሜን::

19ኛ እሱና ሰንሰለቱ ያደረሱት ጥፋትና የፈጸሙት ፀረ መንግስትና ፀረ ሕዝብ ድርጊት ዝርዝሩ ብዙ ነዉና ለጊዜዉ ይብቃን::

## <u>ክፍል ሦስት: ሲዳማ ከርስዎ ምን ይጠብቃል??</u>

የተከበሩ አቶ ደሴ ዳልኬ እርስዎ ከአብራኩ የወጣህ የሲዳማ ልጅ ነህ:: አሁን የተረከብከዉ ፕሬዝዳንትነትም ሲዳማን ወክለህ ቢሆንም ሲዳማን ያለአግባብ ሳትጠቀምና ሌላዉን ያለ አግባብ ሳትጎዳ 56ቱን ብሔር ብሔረሰብ በዘር በሃይማኖትና በሀሳብ ልዩነት አድሎ ሳታደርግ በሕግ አግባብ ብቻ በንፁህ ሕሊና መልካም አስተዳደር እንድታሰፍን ነዉ:: ይህን አድርገህ በሲዳማና በሌላዉ ሕዝብ ስትወደስ የሲዳማ ሕዝብም ይኮራብሃል:: ሺፈራዉ በሲዳማ ብቻ ሳይሆን በሙስናዉና በምግባረ ብልሹነቱ በሌላዉም ሕዝብም ጭምር ተዋርዶ ነዉ የሲዳማንም ሕዝብ ያሳፈረዉ:: ስለሆነም ለሲዳማ በሀገሪቱ ሕገ መንግስት ፖሊሲና እቅድ መሰረት ልያገ የሚገባዉን መብቱን ጥቅሙንና ድርሻዉን ማስጠበቅ ሲሆን ይህ በግልህ የማይቻልህም ከሆነ ሕዝቡ መብቱንና ጥቅሙን ለማስከበር በሕግና በሕግ አግባብ ብቻ በሚያደርገዉ ሰላማዊ ትግል ላይ ከሕግ አግባብ ዉጪ ጣልቃ እንዳትገባ ሆኖ ሲዳማ ከእርስዎ አስተዳደር የሚጠብቃቸዉን ከዚህ በታች የተዘረዘሩትን በቅን ልቦና እንድታስተዉል::

1ኛ የሲዳማ ክልል ዉሳኔን በተመለከተ ዉሳኔዉ እርስዎም በተገኙበትና በፈረሙበት ታሪካዊ ሰነድ በታሪካዊዉ ቀን ሐምሌ 7/1997 የፀደቀ ሲሆን በሺፈራዉና ግልገል ሆዳም ካድሬዎቹ ደንቃራነትና የሲዳማ ሽማግሌዎች ከሟቹ ጠቅላይ ሚኒስቴር ጋር ሲወያዩ ጠቅላይ ሚኒስትሩ በጊዜዉ ከነበረዉ የሀገሪቱ ተጨባጭ ሁኔታ አንፃር የሲዳማ ክልል ዉሳኔ ተግባራዊነት ትንሽ ጊዜ እንድሰጡአቸዉ ጠቅላይ ሚኒስትሩ የሲዳማን ሀገር ሽማግሌዎች በመማፀናቸዉ እስካሁን ብዘገይም ሕገ መንግስታዊዉ ዉሳኔዉ በአጭር ጊዜ ዉስጥ ተግባራዊ እንድሆን ሁለንተናዊ ዝግጅት ተጠናቋል:: ስለሆነም እርስዎ በዚህ ሁኔታ ዉስጥ ምንም የሚያደርጉት የግል

አስተዋጽኦ የለምም::አይኖርምም:: ከርስዎ የሚጠበቀዉ ሕገ መንግስቱ በአግባቡ እንድተረጎም ማድረግና እንደነሺፈራዉ ፀረ ሕገ መንግስት እንቅስቃሴ እንዳታደርግ ብቻ ነዉ::

2ኛ የዘንድሮው ፍቼ በከፍተኛ ድምቀት እንድከበርና በዩኔስኮ እንድመዘገብ ማስደረግ::

የዘንድሮዉ ፍቼ በአል በዚህ በሐምሌ 26 2005 ይከበራል:: ሺፈራዉ በ2004 ፍቼ ቀን በጭሜሳዎችና በሕዝቡ የደረሰበትን ዉግዘት ለመበቀል የዘንድሮዉ ፍቼ እንዳይከበርና ምናልባትም በዉጫዊ ጫና የሚከበር ቢሆንም በለመደዉ የዉሸት ግርግርና ሁኬት መፍጠር ብልጠቱ ራሱ ባዘጋጀዉ ሃይል በእለቱ ሁከትና ግርግር ፈጥሮ ሕዝቡን ለመበቀል ተዘጋጅቶበት እያለ የሲዳማ አምላክ እንደነቀለዉ "እግዚአብሔር ሆይ! ዘንድሮ ሕዝብህን ከምን አይነት እልቀት አወጣሃቸዉ" እያሉ እግዚአሔርን ሲያመሰግኑ እንደነበር ዉስጠ አዋቂዎች ይናገራሉ:: ስለሆነም አቶ ደሴ እሱን ነቅሎ ለሕዝቡ እግዚአብሔር አንተን ስላስቀመጠ አንተም ሆንክ አለምም እንደሚያዉቀዉ የፍቼ በአል በሲዳማ በልዩ ፍቅር ይጠመቃል ይከበራልም:: ስለዚህ ገና ሥራ ከመጀመርህ የገጠመህ መልካም አጋጣሚ ነዉና ሕዝቡ ማንነትህን የሚያዉቅበትንና የሚረዳበትን ትልቅ መድረክ እግዚብሔር ስላዘጋጀልህ ይህን ወርቃማ እድል ተጠቅመህ የዘንድሮዉ የሲዳማ ፍቼ ከመቼዉም ጊዜ በላቀ ሁኔታ በድምቀት; በሰላም: በተረጋጋና ሕዝብን ከመንግስት በሚያቀራርብ ንግግር እንድከበርና በቀጣይነትም የፍቼዉ በአል በአለም ቅርስነት እንድመዘገብ የተጀመረዉን እንቅስቃሴ በማፋጠን የሲዳማ ልጅነትህንና አለ ታነትህን እንድታስመሰክር ወንድማዊ ምክሬን እየለገስኩልህ ለዚህም ተግባራዊነት በቁርጠ ነት በመሥራት ሕዝቡን እንደምትክስና እንደማታሳፍረ በመተማመን ነዉ:: አቶ ደሴ የማናቸዉም ሥራ አጀማመሩ ያማረ ከሆነ መኻሉም ሆነ ፍጻሜዉም የሰመረ ይሆናልና በዚህች ነጥብ ላይ እጅግ እጅጉን አስብበት; አስተዉለህም ፈጽም:: የሲዳማ አምላክ ጅማሬህንና ፍጻሜህን የተሳካ ያድርግልህ!!! አሜን በል እንጂ!!!

3ኛ የሲዳማን የሥልጣን ድርሻ ማስጠበቅ ሲዳማ ባለዉ የሕዝብ ብዛትና ለሀገሪቱ ኢኮኖሚ ከሚያበረክተዉ ድርሻ አንፃር በፌዴራል የምክትል ጠቅላይ ሚኒስቴርነትና ከ4 ያላነሰ የሚኒስትርነት ከ15 ያላነሰ የምክትል ሚኒስትርነትና ኤምባሲነት; በአዲስ አበባ ከ3 የሚበልጥ ቢሮ ሃላፍነትና በክልሉ ደግሞ ከ5 የሚበልጥ ቁልፍ ቢሮ ሃላፍነትና በሁሉም ቢሮ ቢያንስ አንዳንድ ምክትል ቢሮ ሃላፍነት ሥልጣን ይገባዋል:: ለዚህም ከሀገር አልፎ በአለም አቀፍ ደረጃ ተወዳዳሪ የሚሆኑ በሙያቸዉ በብቃታቸዉ በመልካም ስነ ምግባራቸዉ የተመሰከረላቸዉ በሀገር ዉስጥና በአዉሮፓና በአሜሪካ ከታወቁ ዩኒቬርስቲዎች 2ኛና 3ኛ ድግሪ ያላቸዉ በሀገር ዉስጥና በዉጭ ሀገራት በመንግስትና አለም አቀፍ በሆኑ ድርጅቶች ዉስጥ የሚሰሩ ከ3500 በላይ ታዋቂ ምሁራኖች ይጠብቁሃል::

4ኛ ሲዳማ ማግኘት የሚገባዉ በጀት ድርሻ ማስጠበቅ  ሲዳማ ከቡናና ጫት ምርት ብቻ የሀገሪቱን 1/3ኛ የዉጭና የሀገር ዉስጥ ገቢ ይሸፍናል ቢባል ማጋነን አይሆንም:: ግን ሲዳማ ለ22 አመታት ሙሉ ሲመደብለት የነበረዉ በጀት ለሰራተኛ ደመወዝ እንካን በቂ ሳይሆን ቀርቶ ለሰራተኛዉ ከግለሰብ ተበድሮ ሲከፈል እየተስተዋለ ነዉ::

5ኛ የብሔሩን ሕልዉና የሚፈታተኑ ኢ-ሕገመንግስታዊ የሆኑ ትንኮሳዎችን መከላከል:: ከዴህዴን ቢሮ ይሁን ወይም ከነ አቶ አለማየሁና ከአቶ ሺፈራዉ የግል ኮምፕዉተር አይታወቅም በየጊዜዉ የሲዳማን ብሔር ትዕግስት የሚፈታተኑ መሰረት የለሽና ኢ-ሕገመንግስታዊ የሆኑ ሰነዶች ለዉይይት ቀረቡ ይባላል:: ሕዝቡ በነዚህ ትንኮሳዎች ስሜት ዉስጥ ይገባና ትርምስ ይፈጠራል::ካድሬዉና ሰራተኛዉ በነዚህ ሰነዶች ላይ በመወያየትና በማወያየት አብዛኛዉን የልማት ሥራ የሚሰሩበትን ጊዜ የራሳቸዉንም ሆነ የአርሶ አደሩን ሥራ ሲያስፈቱ ይከርማሉ; ከርመዋልም:: ተማሪዉም ከትምህርቱ ይስተጓጎላል:: ለአብነት ያህል በ2004 ከዴህዴን ቢሮ ለዉይይት ቀረበ የተባለዉ ለራሳቸዉም ቢሆን ትርጉሙን በዉል የማያዉቁትን የ"ሜትሮፖልትያን" ሰነድ በማለት የተሰራጨና በዚህም ሳቢያ በሲዳማ ክልል የተፈጠረዉ ሁከትና ትርምስ ይታወሳል:: ግርግር ለሌባ ይመቻልና አጅሬዉ ሺፈራዉ በዚህ ሰበብ ማስትሬቶችን ብቻ እያስለቀመ ከ112 በላይ የሚሆኑትን ምሁራን አሳፈሰ; አሳሰረ:: ግማሾቹ ሀገር ለቀዉለት ኮበለሉ:: ይህ ኢ-ሕገመንግስታዊ ሰነድ አጠቃላይ የሲዳማን ብሔር ከዳር እስከ ዳር አስቆጣ:: ሥራ ቆመ:: ትምህርት ቆመ:: እርሻ ቆመ:: የሕዝቡ ቁጣ ከጫፍ እስከ ጫፍ ምድርቱን ሲያናዉጥ አጅሬዉ አቶ ሺፈራዉ "ይህ ሰነድ የተባለዉ የሌለ ሕጋዊ አይደለም እኔ በሌለሁበት የተሰራጨ ሰነድ ነዉ ያልተነጋገርንበትንና ያልፀደቀ ሰነድ በማዘጋጀትና በማሰራጨት ሁከት የፈጠሩት ባለሥልጣኖች ይጠየቁበታል" በማለት ዴህዴንና ባለሥልጣኖቹን ኮንኖ እሱ ግን የሕዝብ ወዳጅ የሆነ መሰለዉ:: ሰነድ ነዉ ተብዬዉን ሺፈራዉ ራሱ ለዉይይት አቅርቡ በማለት ወደ ዉጪ እንደሄደና ካለበትም ሀገር ሆኖ በየደቂቃዉ ለካድሬዎቹ መመሪያና ትዕዛዝ እየሰጠ ሂደቱን ይከታተል እንደነበር ይታወቃል:: ያ ሁሉ ሰዉ ከሹመትና ከሥራ ከተባረረ; ከታሰረና ከታጎረና ቢያንስ ለሦሥት ወራት በክልሉ የመንግስትና የሕዝብ ሥራ ተስተጓጉሎ "ሰነዱ ከመንግስት የቀረበ አይደለም|" ማለት የምን ድራማ ነዉ? ሰነዱ ከድርጅትና ከመንግስት ቢሮ ካልወጣ ሰነዱን ይዘዉ ቢያንስ ለ2 ወራት በተለያዩ የካድሬና የመንግስት ሰራተኞች መድረክ ሲያወያዩ የነበሩና በዚህ ሐሰተኛና ኢ-ሕገ መንግስታዊ የሕዝቡን ሕልዉና የሚፈታተንና የሚያዋርድ ሰነድ በማሰራጨት ለዚያ ሁሉ ሁከት ብጥብጥ ሥራ መፍታት እስራትና እንግልት መንስኤ የሆኑ ባለሥልጣኖች ላይ ምን እርምጃ ተወሰደ? ሌላዉ ለአብነት የሚጠቀሰዉ ካለፉት 3 ወራት ወዲህ እየተናፈሰ ያለዉ ዉዥንብር "የሐዋሳ

ከተማ ለፌዴራል ተሰጠች; የሲዳማ ክልላዊ መንግስት መናገሻ ከተማ ከሐዋሳ ዉጪ ልሆን ነዉ የከተማዋ አስተዳደር በስብጥር ልሆን ነዉ ወዘተ" በማለት የሕዝቡን ስሜት በመፈታተን ላይ ናቸዉ:: እንደዚህ አይነት ዉዥንብሮች ለአመታት እየተነዙ የቆዩ ቢሆንም በሕዝቡ ቁጣ እየተመለሱ ቆይተዋል:: እንደዚህ አይነት ኢ-ሕገ መንግስታዊ ሰነዶችና ዉዥንብሮች አሁንም ሆነ ወደፍት በሲዳማ ሕዝብ ዘንድ ቦታ አይኖራቸዉም:: እነዚህ ዉዥንብሮች በሲዳማ ምድር ተግባራዊ የሚሆኑት እናት ማህፀን ዉስጥ ካለዉ ጽንስ ጀምሮ 6,7ቱም ሚልዮን ሕዝብ በጅምላ ጨራሽ ኬሚካል መሳሪያ ዶግ አመድ ሲደረግ ብቻ ነዉና ይህንን ተገንዝበህ የማይሆኑ ግን ሕዝብን ከመንግስት በማራራቅ ያንተንም ሆነ የሌሎችን ማንነት የሚያጎድፉና ቀጣናዉን ከልማት ቀጣናነት አዉጥተዉ በካድሬዎች ሰራሽ ሽብር እንዳይበጠበጥ ማንኛዉም ሰነድ ለሕዝብ ይፋ ከመደረጉ በፍት ከፍተኛ ጥንቃቄ እንድወሰድበት አድርግ ::

6ኛ የክልሉ ፍትሕ ጠቅላይ ፍርድ ቤትና አቃቤ ሕግ አካላት የፀረ ሙስናና የፖሊስ ኮሚሽን ሃላፍዎችና ኦፍሴሮች ከፀረ ሲዳማ ድርጊታቸዉ እንድታቀቡ ማድረግ::

ለመሆኑ የነዚህ መሥሪያ ቤቶች ሃላፍዎችና ኦፍሴሮች በሲዳማ ብሔር ላይ እንድሰሩ ብቻ ነዉ የተመደቡት?? ደቡብ ክልል ማለት ሲዳማ ብቻ ነዉ?? ለክልሉ ፀረ ሙስና ኮሚሽን እነሱን የሚያጣራ ሌላ ፀረ ሙስና ኮሚሽን መቋቋም አለበት እየተባለኮ ነዉ በሕዝቡ:: የክልሉ ፍትሕ ;ጠቅላይ ፍርድ ቤትና አቃቤ ሕግ አካላት ወዘተ ሃላፍዎችና ኦፍሴሮች እነማን ሆኑና ነዉ?? የእያንዳንዳቸዉ ፋይል ከፈለጉ ይነበብላቸዋልኮ:: ለመሆኑ እነዚህ ጉዶች ከተቀጠሩ አመት ሳይሞላቸዉ የፀረ ሙስና; የአቃቤ ሕጎች; የዳኞች; ወዘተ እየተባለ በሕዝቡ በይፋ በተሰየሙ መንደሮች የተንጣለሉ ቪላዎችን የገነቡት ወይም ያስገነቡት ከየት አምጥተዉ ነዉ?? ስለሆነም በተልዕኮ በአንድ ብሔር ላይ ብቻ የሚያነጣጥሩትን የመንግስት ሃላፍዎችንና ኦፍሴሮችን ከሲዳማ ብሔር ላይ እጃቸዉን እንድያነሱ ተግሳጽ ልሰጣቸዉ ይገባል::

7ኛ ልማትን ማፋጠንና ሥራ አጥነትን መቀነስ:: ከላይ እንደተጠቀሰዉ ሺፈራዉ ለሲዳማ "ልማት አያስፈልገዉም ሁሉም ነዋር ሚሊየነር አድርገነዋል" በማለት ሕዝቡን ሲበቀል ከርሟል:: ስለሆነም ከ6.7 ሚሊየን ሲዳማ ከግማሽ በላዩ በፍፁም ድህነት ዉስጥ ተዘፍቆ ይገኛል:: ስለሆነም የተከበሩ አቶ ደሴ ሌላዉ እያደረገ እንዳለዉ ረሀብን ሸሽተዉ መጥተዉ አስተዋሽ አጥተዉ የነሱ አንጡራ ሀብት እየተዘረፈ ለሌላ ሲሳይ ሲሆን የበይ ተመልካች ሆነዉ በገዛ ቀያቸዉ በሐዋሳ ከተማ ብቻ ከ15000 በላይ ለልመናና ለጎዳና ተዳዳርነት ከተዳረጉት ሕፃናትና አቅመ ደካማ አሮጊቶች አንስቶ በሲዳማ በሁሉም መንደር በረሀብና በሥራ አጥነት እየተሰቃዩ ያሉትን ሁሉ ከመንገድ ዳር ንግድ አንስቶ በገጠርም በከተማም በጥቃቅን

በማደራጀት በመንግስት መሥሪያ ቤቶች ከሙያ እስከ ጉልበት ሰራተኛነት ተገቢዉን ድርሻ በማስገኘት በተለይም በአካባቢዉ ባሉ የመንግስትና የግል በፋብሪካዎች በሕጉ መሰረት በአብዛኛው የሥራ መደብ በተለይም ልዩ ሙያ ከማይጠይቁ መደቦች ዉጭ ያለዉን ሁሉ የአካባቢዉ ሕብረተሰብ ተጠቃሚ እንድሆን መመሪያ በማስተላለፍ በተወሰነ የሙያ ስልጠና ወደ ሥራ እንድገቡ ወዘተ በማድረግ እንድታደጉአቸዉ:: ይህንን ለመፈፀም ሀሳቡና ተቆርቀርነቱ ካለ የመንግስት በጀትም አለ:: የሲዳማ ሀብት እንካን ለልጆቹ ለሌላዉም ተርፎት የለም እንዴ?

8ኛ ከሺፈራዉ ሰንሰለት ራስህን ማራቅ   አቶ ደሴ በሙስናና በሥነ ምግባር ብሉሹነት ሕዝቡን ያማረረዉ አንድ ሺፈራዉ ብቻ ሳይሆን በሁሉም የመንግስት የሕዝብና የሃይማኖት ተቀማት ከላይ እስከ ታች የተሰገሰጉ ምልምሎች ጭምር ናቸዉ:: በሺፈራዉ የሙስናና ዘረፋ ሰንሰለት ዉስጥ ባለሀብት ነን ከሚሉት ደላላዎች አንስቶ ሐሰተኛ ነቢያትና ሰባኪዎች ፀጉራቸዉ የተመለጠና የሸበተ ወራዳ ሽማግሌዎች ወዘተ በመንግስት መስሪያ ቤቶች በተለይም በሐዋሳ ከተማ ማዘጋጃ በቤቶች ልማት በክልል በሲዳማ ዞን በወረዳዎችና በቀበሌዎች በሐዋሳ ከተማ በክፍለ ከተማዎች በኮንስትራክሽን በንግድ በፋይናንስ በገቢዎች በፍርድ ቤቶችና በፖሊስ መስሪያ ቤቶችና በሲዳማ ልማት ድርጅቶች ማለትም በሲዳማ ማይክሮ ፋይናንስ በSDC በፉራ በሲዳማ ልማት ማህበር በስፖርት ክለቡ ወዘተ ተሰግስገዉ ይገኛሉ:: እነዚህ የጥፋትና የዘረፋ ቡድኖች ምንም ሥራ የማይሰሩ ልሰሩም ችሎታዉና ብቃቱ የሌላቸዉ የሚንደላቀቁት ለአለቃቸዉ ለሺፈራዉ ከጉቦ ጋር ሐሜትና ወሬ በማመላለስ ሕዝቡን ያማረሩ ተምቾች ናቸዉ:: እነዚህ ዘራፍዎች ሕዝቡን ለማደናገርና አለን ለማለት ያህል ለአለቃቸዉ መባረር ሐምሌ 5/ 2005 በቤተ መንግስት ባዘጋጁት የ "ምስጋና ፕሮግራም" ላይ ከአለቃቸዉ በተሰጣቸዉ ትዕዛዝ አንተን በተለያዩ ዘዴዎች የሰንሰለቱ አባል ልያደርጉህ ወጥመድ አዘጋጅተዉልህ ነዉና ያሉት አስተዉለህ ተራመድ::

9ኛ በሀዋሳ ከተማና በዞኑ ወረዳዎችና ክፍለ ከተማዎችና ቀበሌዎች መዋቅር ላይ ችሎታና አቅም ያላቸዉን ከሁሉም ወረዳ በተመጣጣኝ መልኩ ማስቀመጥ    ሕዝቡን ካስመረሩት መልካም አስተዳደር እጦቶች ዉስጥ በሁሉም እርከን ላይ ከአንድ ቤተሰብ ለዚያዉም ምንም ችሎታ የሌላቸዉ ሲሾሙና ሲመደቡ በተሾሙበትና በተመደቡበት ሃላፍነትም የአንድን ጎሳ ወይም የመጡበትን አካባቢ ጥቅም ብቻ እያስቀደሙ አብዛኛዉን ሕዝብ መንግስት የለም እንድል አድርገዉታልና ይህንን አሰራር ለማጥፋት ሥራ::

10ኛ አሁን እየተሰራ ያለዉ የሹመትና የሥራ ምደባ ሁሉንም ወደ መጣበት ወረዳ ወይም ጎሳ መላክ ሲሆን ይህ አሰራር ቀርቶ ማንም በየትኛዉም ወረዳ ሂዶ መሥራት አለበት::

11ኛ በበታችነት ስሜት የሚዳክረዉ ሺፈራዉ በምቀኝነትና በፍራቻ ፖለቲካ ተማረዉና ተገፍተዉ ሲዳማንና ክልሉን ለቀዉ በሌሎች ክልሎችና በዉጭ ሀገራት ያሉትን በእዉቀታቸዉና በችሎታቸዉ በወገን አለኝታነታቸዉ ድፍን ሲዳማ እንደ አይኑ ብሌን የሚያያቸዉ ታዋቂ ምሁራንን መመለስና በክልል በአዲስ አበባና በፌዴራል መዋቅር ዉስጥ በማስገባት ለሲዳማ ለክልሉና ለሀገራቸዉ እንድያገለግሉ በማድረግ በሺፈራዉ ተባረዉ ከሄዱ ምሁራኖች ጋር አብሮአቸዉ የሸፈተዉን የሕዝቡን ልብ በመመለስ መመኪያ ልጆቹን ከአጠገቡ አጥቶ በሀዘን ዉስጥ ያለዉን ሲዳማ ለማፅናናት የተቻለህን ሁሉ አድርግ::

12ኛ የሀገርና የጎሳ ሽማግሌዎችን በአካባቢያቸዉ ሕዝብ ባለቸዉ ተሰሚነትና ተቀባይነት መልካም ሥነ ምግባር መመልመልና ከሀሰተኛ የሀይማኖት ሰባኪ መሪና ነቢያት ነን ከሚሉት ራስህን ማራቅ::

13ኛ በተለይም በተለይም የድሃዉን ሕዝብ ኪስ በማራቆትና ፍትሕን እንደ ሸቀጥ በገንዘብ በመሸጥ ሕዝብ መንግስትን እንድያማርርና መንግስት የለም ብሎ መንግስትን እንድጠላ ባደረጉ በሁሉም እርከን ላይ ባሉ የፍትህና የፖሊስ የከተማና የገቢዎች ወዘተ መዋቅር ሹመኞች ላይ ጠበቅ ያለ እርምጃ በመዉሰድ ሕዝብንና መንግስትን ለማቀራረብ ጥረት አድርግ::

14ኛ ብዙ ችግር እንዳለበት የሚነገርለትን የቡናና የጫት ግብይት ሥርአት በማስተካከል የሲዳማ ገበሬና ነጋዴ አግባብነት ያለዉን የምርቱን ዋጋና ነጋዴዉም የልፋቱን ትርፍ እንድያገኝ ከሚመለከታቸዉ አካላት ጋር የችግሩን አሳሳቢነት በመነጋገር የገበያና የንግድ ፍሰቱ ከጥቂቶች ቁጥጥር ተላቆ ነፃ ዉድድር የሰፈነበት እንድሆን ጥረት ማድረግ: :

15ኛ በጥቃቅን ማህበራት ሽፋን ሕገወጥ የመንገድ ዳር ግንባታና ንግድ እንድወገድ በማድረግ እስካሁን በእድሉ እንዳይጠቀሙ ዳር ተገፍተዉ ለጎዳና ተዳዳርነት የተዳረጉትን ማደራጀትና ወደ ሥራ ማስገባት::

16ኛ ለጥቃቅን ንግድ ተብሎ በየመንደሩ የተገነቡ ቤቶች በአሁኑ ጊዜ በሕገ ወጥ አሰራር ወደ መኖሪያ ቤትነት ተቀይረዉ ያሉትን ለተገነቡበት አላማ እንድዉሉ በማድረግ ሥራ አጥነትን መቀነስ::

17ኛ የሐዋሳ ዩኒቬርስቲና ሪፌራል ሆስፒታሉ የሲዳማ ነዉ በሁሉም ዩኒቬርስቲዎች እየተደረገ እንዳለዉ ከጉልበት ሰራተኛና እስ ከሙያተኛ መደብ ከአስተዳደር እስከ አካዳሚ ስታፍ ያለዉ ሃላፍነትና መደብ ለብሔሩ እንድሰጡ:: በነዚህ ተቀማት በርካታ ጉዳዮች እየተከናወኑ ነዉና::

18ኛ ሌላዉ ትልቅ ትኩረት ልሰጠዉና መስተካከል የሚገባዉ ጉዳይ ሲዳማ ለክልሉ በላይ ገቢ ያስገባል:: ግን በየአመቱ የሚመደብለት በጀት ከደመወዝ ያላለፈ ነዉ:: ይህንንም ከግማሽ በላዩን የደመወዝ በጀት እየተጠቀሙ ያሉት ከሐዋሳ ከተማ አንስቶ በሁሉም የሲዳማ ወረዳዎችና የከተማ መሥሪያ ቤቶች በክልሉ ያሉ ሹመኞችና ካድሬዎች ሚስቶችና ዘመዶች ናቸዉ :: እነዚህ ቅምጥሎች በወር አንዴ እንካን በሥራ ገበታቸዉ ላይ አይገኙም:: ማንስ ተቆጣጥሮአቸዉ?? ሲዳማ ከበጀቱም ከሥራም አልሆነም:: አብዛኛዎቹ ቅምጥሎች ከዲፕሎማ ያለፈ ትምህርት የላቸዉም:: በሌላ በኩል ደግሞ እናት አባታቸዉ ያለዉን ጥርት በማሟጠጥ በዲፕሎማና በዲግር ተመርቀዉ ሥራ አጥ የሆኑ በ10ሺዎች የሚቆጠሩ አሉ::

19ኛ በሐዋሳ ከተማና በሲዳማ በሁሉም ወረዳዎችና ከተማዎች በርካታ የመንግስትና የግል ባንኮችና ኢንሹራንስ ኩባንያዎች ይገኛሉ:: በነዚህ ኩባንያዎች ዉስጥ አንድም የአካባቢዉ ሰራተኛ የለም:: የኩባንያዎቹ ሥራ ይህን ያህል ዉስብስብና የተለየ ሙያ የሚጠይቅ ሆኖ ሳይሆን የኩባንያዎቹ መዋቅር ከላይ እስከ ታች በሰንሰለት የተያያዘ ስለሆነና የአካባቢዉ ሙያተኛ የመወዳደር እድል ልያገኝ  ባለመቻሉ ነዉ:: በሌላ በኩል ደግሞ የነዚህ ባንኮችና ኢንሹራንሶች ከ2/3 ኛዉ በላይ  የቁጠባና የብድር ተጠቃሚ ደንበኛ የአካባቢዉ አርሶ አደሮች; ነጋዴዎችና ባለሀብቶች ናቸዉ :: ስለሆነም ቀስ በቀስ ይህም መስተካከል ያለበት አጀንዳ ነዉ::

20ኛ የገጠር መሬት ወረራ መቆም አለበት  አቶ ደሴ በአሁኑ ጊዜ በጣም በሚያሳዝንና በሚሰቀጥጥ ሁኔታ በሐዋሳ ከተማ አቅራቢያ ያሉ አርሶ አደሮች በመታለልና ባልሆነ ዉዥንብር በመወናበድ መሬታቸዉን ተቀምተዋል:: በዚህ ሴራ ዉስጥ ከማዘጋጃዉ ባለሙያዎች ጭምር የተሳፉበት የደላላዎች መዋቅር አለ:: ስለሆነም ይህ ሕገ ወጥ የአርሶ አደሩ መሬት ዘረፋና ወረራ እርምጃ ተወስዶበት በአርሶ አደሩ መሬት ላይ በሕገ ወጥ መንገድ የተገነባዉ የጨረቃ ቤቶች ግንባታ እንደ ሌላዉ የሀገሪቱ ከተማዎች ፈርሶ አርሶ አደሩ የተዘረፈዉ መሬቱ ባለቤት መደረግ አለበት::

21ኛ የሐዋሳ ከተማ መሬት ወረራ መታገድ አለበት አቶ ደሴ ሺፈራዉ እስካሁን ድረስ በሥልጣን የቆየዉ የሐዋሳን ከተማ መሬት ከፕላንና ከሊዝ ፖሊስዉ ዉጭ በመቸብቸብና ለፈለገዉ በፈለገዉ መጠን የመኖርያና የንግድ መሬት እየሰጠ በመደለልና በማታለል ነዉ:: የሐዋሳ መሬት ባይኖር ኖሮ የሲዳማ የክልል ዉሳኔም አይዘገይም ነበር:: የሲዳማ መሬት መልሶ ለሲዳማ ጠላት ሆነ:: የክልል ዉሳኔዉን አክሽፈናል ለማለት ካድሬዉም; ደላላ ነጋዴዉም; የጎሳና የሃይማኖት መሪዎች ነን ባዮችም ወዘተ የደፈሩት ሺፈራዉ የሐዋሳን መሬት እየሰጣቸዉ ነዉ:: ከሺፈራዉ መሬት ለመዉሰድ የሲዳማን ክልል መቃወምና ስለ ዉሳኔዉ ትክክለኛነት

የሚያነሱትን በመኮንንና በማስወንጀል ነው:: የሐዋሳ መሬት ባይኖር ኖሮ ሺፈራው በዚህ ሁሉ ፀረ ሕዝብ እርምጃዉና ብልሹ ሥነ ምግባሩ አንድ አመት እንካን አይቆይም ነበር:: አቶ ደሴ ስለ ሐዋሳ መሬት ሕገወጥ ዘረፋ እንካን አንተ አለም ሁሉ የሚያዉቀዉ ጉዳይ ነዉና ስለቆየዉ ዘረፋ ሳይሆን በቅርቡ ከ3 ወራት ወዲህ ስለሆነው ድፍረት የሞላበት ዘረፋ ልጥቀስልህ:: አዲስ የከተማ ቦታ ሊዝ አዋጅ ወጥቶ በሕዝቡ ዘንድ ተቀባይነትን ባለማግኘቱ ተግባራዊ ሳይሆን መቆየቱ ይታወሳል:: አቶ ሺፈራው ግን የሲዳማን መሬት ሳይቸረችር አንዲት እስትንፋስ መተንፈስ አይችልምና ከ3 ወር በፍት የመኖሪያና የንግድ ቦታዎችን ማዘጋጃ ቤት ባስቀመጠዉ ልቅ ዘራፍና አዘራፍ አማካይነት ለሊዝ እንድቀርቡ አደረገ:: በነሱ ቤት ሕጋዊ ነው በማለት በሰነድ ከቸበቸቡት ቦታዎች በርካታ ሚሊዮኖችን አጋበሱ:: ይህ ሽፋን ነበር:: እነ ሺፈራዉና ሰንሰለቱ በዚህ ሽፋን ሌላ ሕገወጥ የዘረፋ ስልት አዘጋጅተዉ ኖሮ በሰነድ ለጨረታ በቀረቡ የንግድና የመኖሪያ ቦታዎች ሽፋን ከ113 በላይ የሚሆኑትን የንግድና የመኖሪያ ቦታዎችን እያንዳንዳቸዉ ከ3 እስከ 10 የሚደርሱትን ተቀራመቱ:: በሊዝ የተሰጡ ቦታዎች ናቸዉ እየተባለ ይዞታቸዉን አስከበሩ; አሳጠሩ; ግንባታም አስጀመሩ:: ታዲያስ አቶ ደሴ ይህ አይን ያወጣ የትናንትና ሌብነትና ዘረፋ ወሬ ጭምጭምታ እስካሁን አልሰማህም ማለት ይቻላል?? ስለዚህ ምን ለማድረግ ነዉ ያሰብከዉ?? በጠራራ ፀሃይ የተዘረፈዉ የመንግስትና የሕዝብ መሬት ተመልሶ ዘራፍዎቹ ከሺፈራዉ ጭምር ለሕግ መቅረብ የለባቸዉም ነዉ የምትለዉ??

22ኛ በተቻለህ ሁሉ ነፃ የትምህርት እድል በመስጠት ሆስቴል በማዘጋጀት የተለየ ማበራተቻ በመስጠትና በልጅነታቸዉ እንዳያገቡ በማስተማር ወዘተ ለሴት ተማሪዎች ትምህርት ትኩረት መስጠት::

23ኛ በተለያዩ የሙያ ዘርፎች የሚያግዙህንና የሚያማክሩህን ምሁራንና የእድሜ ባለፀጋዎችን በራስህ መመዘኛ መርጠህ አንዳንድ ጉዳዮችን ማማከር መመካከር::

24ኛ በአንድ ዉድ የሲዳማ ልጅ ተመስርተዉ በሁሉም ረገድ በሀገርና በአፍሪካ አልፎም በአለም ሞዴል የነበሩ የሲዳማ ልማት ድርጅቶች የ1994 በሀይለ ማሪያምና የሺፈራዉ ጭራቅ መንግስት ይህንን ዉድና ሌሎች የሲዳማ አለ ታ ምሁራንን በማሳደድ ከሀገር እንድሰደዱ በማድረግ ሺፈራዉና መሃይማኑ ካድሬዎቹ የሲዳማን ልማት ድርጅቶች ፉራ ማሰልጠኛ ተቀም; ፉራ ት ቤት; SDC; ሲዳማ ልማት ማህበር; ሲዳማ ማይክሮ ፋይናንስ; አዳሬ ኢንጂኔርግንና የአበባ እርሻን እያንዳንዳቸዉን ከመቶዎች ሚሊዮን ጥሬ ገንዘብና ቀሚና ተንቀሳቃሽ ንብረት ጋር ሺፈራዉና የተምች ቡድኑ በ1994 ተረክበዉ ራሳቸዉ ቦርድ; ሥራ አስኪያጅ; ሂሳብ ሹምና ገንዘብ ያዝ በመሆን ዘመድ አዝማዳቸዉንና የጥቅም ወዳጆቻቸዉን እያፈራረቁ ሲመዘብሩት

ቆይተዋል:: ሌላዉን የ11 አመቱን ታሪክ ሳናነሳ በ2005 ከ3 ወራት በፍት ለአንድ ወር ብቻ የተሾመዉ በዚህ በአንድ ወር ብቻ 8 ሚሊየን የድርሻዉን መዉሰዱን በሕዝብ ዜና ማሰራጫ በድፍረት ሲያዉጅ ዜናዉን የሰማዉ ከሲዳማ ብሔር ዉጭ ያለዉ የከተማዉ ሕዝብ ባሰማዉ ጩሄት ዘራፍዉን ከዘረፈዉ 8 ሚሊየን ጋር የት እንደሰወሩት አልታወቀም:: ይህ የቅርብ ዘረፋ ስለሆነ ተነሳ እንጂ በ11 አመታት ዉስጥ የተዘረፈዉን ከዚህ ከአንድ ወር ዘረፋ አንፃር ማገናዘብ ይቻላል::

ስለሆነም አቶ ደሴ 1ኛ ከ1994 ጀምሮ ያለዉ የነዚህ ልማት ድርጅቶች በእዉቅ ገለልተኛ ኦዲት ድርጅቶች በአስቸካይ እንድሰራና ጉዱ ለሕዝብ ገሃድ ሆኖ ድርጅቶቹ በፕሮፍሽናሎች እንድመሩ 2ኛ ይህ የማይሆን ከሆነ ድርጅቶች በአጠቃላይ ተዘግተዉ ሀብትና ንብረታቸዉ ለመንግስት ገቢ ይደረግ ::

25ኛ ከሁሉም ከሁሉም ከሐሜትና ከወሬ ራስህን ጠብቅ

ሺፈራዉን በሕዝብ ዘንድ እንድጠላና እንድዋረድ ካደረጉት ከላይ ከተጠቀሱት ድርጊቶቹና ባህርያቶቹ ይበልጥ የሚያስኮንነዉ አስነዋር ዉሸታምነቱና ሐሜተኛነቱ ነዉ:: ሐሜት የሚያመላልሱ በሐሜት ብቻ ከቀበሌ እስከ ፌዴራል ባሉ ከፍተኛ ሃላፍነት ላይ ከተሾሙት አንስቶ በሙያና በተላላኪነት የተመደቡ ሰራተኞች; ደላላ ነጋዴዎች; ሽማግሌዎች; ሀሰተኛ ሰባኪና ነቢይ ነን ባዮች ጭምር ለሱ የዉሸት ወሬና ሐሜት የሚያቀባብሉ ናቸዉ:: በመንደር; በሰፈር; በሥራ ቦታ; በትምህርት ቤት; በመሸታ ቤት; በሴትኛ አዳር ሴት; በቤተ ክርስቲያን ወዘተ ከነሱ ጋር የተጋጨዉን ወይም የሚበልጣቸዉን በቅናትና በምቀ ነት መንፈስ ተሞልተዉ ለሐሜት ረሀብተኛዉ ለሺፈራዉ የፖለቲካና የመንግስት አጀንዳ በማስመሰል ያቀርቡለታል:: እሱም ይደሰትና ሹመት; ሥልጣን; የከተማ ቦታ ይሸልማቸዋል:: ሌላዉም ይከተላል:: የጠላዉን በዉሸት አሽሮ; ከሥራ አስባርሮ; አስገድሎ; አሳስሮ ወዘተ በምትኩ ከሺፈራዉ የሹመት; የከተማ ቦታ; የሥልጣን ወዘተ ስጦታ ለራሱና ለፈለገዉ ዘመዱና ጓደኛዉ ተሸክሞ ይወጣል:: ሐሜተኛ እንካን መሪ ጎሬቤትም ልሆን አይገባዉም:: ቢሆንም መጨረሻዉ ጥላቻና ዉርደት ነዉ:: ስለሆነም አቶ ደሴ የሐሜትና የዉሸታሞች ሰንሰለት አሻንጉሊት እንዳትሆን እነዚህ በየመዋቅሩ ያሉ የሺፈራዉ የሐሜት ቅብብሎሽ ከአለቃቸዉ ጋር እንደለመዱትና እሱም በሰጣቸዉ አመራር መሰረት አንተን ከማንም ቀድመዉ የሰንሰለቱ አባል ለማድረግ እየተሽቀዳደሙብህ ነዉ:: አብዛኛዎች በሱ ጊዜ እንደተበደሉ በመሆን አንዳንዶቹ ደግሞ የመንግስትና የፖለቲካ አጀንዳ በማስመሰልና ይህም አልሳካላቸዉ ሲል እዉነተኛ ሰባኪና ነቢይ በመሆን የዉሸትና የሐሜት ጎርፍ በማዥጎድጎድ ሊያጨናንቁህና ልፈትኑህ ከተሳካላቸዉም የሺፈራዉን ለጋሲ በማስቀጠል እነሱ ጥቅማቸዉን እያስከበሩ አንተን ምናልባትም ከሺፈራዉ በበለጠ ሁኔታ ሕዝቡ

እንድጠላህና እንድተፋህ በማድረግ "ይሄው አላልንም" እያሉ ልዘባበቱብህ እየተሸቀዳደሙ ነዉና ራስህን አዘጋጅተህ ጠብቅ:: በዚህ አንድ ሳምንት በማይሞሉ ቀናት ዉስጥ ስንቱን እንዳስተናገድክ አንተው ታዉቃለህ:: የመጨረሻ መጨረሻ ከምንምና ከማንኛዉም ድርጊትና ባህርይ በማንኛዉም ሥፍራና ሕዝብ ፍት እንደ ሺፈራው አንገት የሚያስደፋህና የሚያዋርድህ የወሬና የሐሜት ሱስ ካለብህና በዚህ ሐሜት ተጠምደህ እዉነትና ሐሰቱን ሳትመረምር በጅምላ የሚትሾምና የሚትሽልም እንዲሁም በምቀ ነት መንፈስ ተሞልተህ ሰዉን የሚትጠላ; የሚትሽር; የሚታባርር; በጭፍን የምትወነጅል; የምታሳፍን; የምታሳስር; የምታሸማቅቅ; የምታስፈራራ ወዘተ ከሆነ መዉደቂያህ ቅርብ አወዳደቅህም ታላቅ ነው የሚሆነዉና ለሁሉም የእናትህ የአባትህ አምላክ ይርዳህ:: አሜን አትልም???

ማጠቃለያ

የተከበሩ አቶ ደሴ ከላይ እንደተጠቀሰው በሲዳማ ዉስጥ ከወረዳ እስከ ዞን አስተዳዳርነት ድረስ በተለያዩ የሃላፍነት ቦታዎች ስትሰራ ስምህ በመጥፎ አልተነሳም:: በጥሩ ሥነምግባር ስትመራ ነበር:: በሙሰ ነትና በሕዝብ ደም አልተጨማለክም:: የሲዳማን ክልል ዉሳኔ ለማኮላሸት በወቅት ከነበሩ ካድሬዎች ጋር ያዙኝ ልቀቁኝ አላልክም:: በነሱ ቤት የሲዳማን ክልል ዉሳኔ አኮላሸነው ብለው ለዚያም ፀረ ሕዝብ ፋከራቸው የተቃዉሞ ጽምፅ ያሰሙትን የ1ኛና 2ኛ ደረጃ ሕፃናት ተማሪዎችን ደም አፍሰው የተሸለሙትን የከተማ ቦታ በሲዳማ ባህል "የወንድምና እህቶቸቹን ደም ላፈሰሰ የሚሰጠው ቁምጥናና የሥጋ ደዌ ነው በማለት አባቴ በሕፃንነቴ ነግሮኛልና አልወስድም" ብለህ እንዳልወሰድክና የወሰዱቱ ባልደረቦችህ በመንግስት እንደሙስና ተቆጥሮ አብዛኛዎቹ ካሉበት ሥልጣን ተባረዉና ታስረው በሕዝብ ፍት እየተሸማቀቁ ሲሄዱ አንተን ግን የእዉነትና የሲዳማ አምላክ ምርቃት አብሮህ ስለነበር ይሄው ያኔ ከነበርክበት በየአመቱ ደረጃህ ከፍ እያለ አሁን እዚህ ደርሰሃል:: ስለሆነም አቶ ደሴ ከላይ የተዘረዘሩትን **Do and Don't** ነጥቦችን በጥንቃቄ አስተዉለህ ንፁህ ሕሊና ይዘህ በሕግ አግባብነት ማድረግ የሚትችለዉን ብቻ አድርግ:: ሕሊናህን ለጥቅምና ለስልጣን አሳልፊህ ሸጠህ የሲዳማንም ሆነ የክልሉን ሕዝብ መብትና ጥቅም አሳልፊህ አትስጥ:: እዚህ ላይ ምርጫው ያንተና ያንተ ብቻ ነው:: የምን ሕዝብ ነው የምትለኝ እነ ሺፈራው ምን ተደረጉ ካልክም ምርጫህን ማንም አይጋፋህም:: ግን ከራስ ጥቅም ይልቅ የሕዝብን ጥቅም ብታስቀድም ሕሊናህ እረፍት ያገኛል ኑሮህ ደስተኛ ይሆናል አንተም ሆንክ ልጅ ልጆችህ በሕዝብ ፍት አንገታቸዉን አትደፉም:: ለፍርፋሪ እንጀራና ሥልጣን ሕዝብን የጨፈጨፉና ያስጨፈጨፉ ያሰሩና ያሳሰሩ የሰደቡና ያሰደቡ ያዋረዱና ያስዋረዱ ወዘተ ከሕዝብ ተለይተው ከአደባባይ ሸሽተው በየስርቻው እየተሽሎከሎኩ በጭንቀትና በአእምሮ ሕመም እየተሰቃዩና የነሱ እርግማን ከነሱ አልፎ

በልጆቻቸዉና¸ በቤተሰባቸዉ ላይ እየደረሰ የሕዝብ እንባ በቁም እየተፋረዳቸዉ ይሄዉ ስንቱን አሳየን እድሜ ዘልዛለዉ:: በሌላ መልኩ ደግሞ ይህንን ሥርአት እያገለገሉ ግን ሕዝብን የእዉቀታቸዉንና የችሎታቸዉን ያህል በሕግ ማዕቀፍ ዉስጥ ሆነዉ በንፁህ ሕሊና አገልግለዉ የሕዝብ ምርቃት በሥርአቱ ከተጣሉበት የአንበሳ ጉሮሮ አዉጥቶአቸዉ ልጆቻቸዉንና ቤታቸዉ ተባርከዉላቸዉ በኑሮአቸዉም ከማንም ያነሰ ሕይወት ሳይኖሩ እነሱም ሆኑ ልጆቻቸዉ እናት አባታቸዉ በሄዱበት ሁሉ ሕዝብ መልካም ከበሬታ እየሰጣቸዉ በሰላምና በኩራት በሕዝብ መካከል ያለምንም ስጋት ፍርሃትና መሸማቀቅ ሲመላለሱ አቤት ሲያስቀኑ:: ከዚህ በላይ ምን ደስታ ይኖራል? እህስ አቶ ደሴ የቱ ይሻልዎታል?????????????????????????????????????????????????????

አቶ ደሴ ይህ ሁሉ ለአንተ ተብሎ ነዉ:: ተጠቃሚዎች አንተና መንግስት ናችሁ:: ሲዳማ አይቀበልም:: ለፈለገዉ የታንክና የአዳፍኔ ጋጋታ አይንበረከክም:: እንካን በ21ኛዉ ክፍለ ዘመን በጨለማዉ ዘመንም ሲዳማ መብቱን የማንነት ክብሩን ለወራር ሃይል አሳልፎ አልሰጠም:: የቅርብ ጊዜዉን የሲዳማን በመሪዉ የፓለቲካ ድርጅቱ ሲአን እየተመራ ያደረገዉን ፀረ ደርግ ተጋድሎንና ጀግንነቱን ማንሳት ይቻላል:: ሲዳማ እንግዳ አክባርና በምድሩ ከልመና እስከ ጉልበት ሥራ በመሰማራት የሚገኘዉን የሌላዉን ብሔር ሕዝብ በዳበረ ባህሉ መሰረት የራሱ ዜጋ አድርጎ በመቀበል ማንኛዉንም የሲዳማ ብሔር ዜግነት ጥቅም ከማንም እኩል እንድካፈል ተደርጎ ይኖራል አቶ ደሴ ይህ እዉነታ ለአንተ ልነገር የሚገባዉ አይመስለ ም:: ሆኖም ግን ደግነቱን ለጋስነቱን አክባሪነቱን ወዘተ በማወቅም ሆነ ባለማወቅ በተሳሳተ ሁኔታ በመተርጎምና የእንግድነት ድንበራቸዉን በመጣስ ከሳሎን ወደ እልፍኝ ዘዉ ብለዉ ለመግባት አጉል ድፍረትን ለማካሄድ እየቃጡ ባሉና በእቅድ ላይ ባሉም ሁሉ ላይ እንደ ሌላዉ አካባቢ አካላዊ ጉዳት ሳያደርስ በባህሉ መሰረት በአክብሮት እንደተቀበለዉና እንዳስተናገደዉ በአክብሮት ይሸኝዋል:: ሲዳማን በተፅዕኖ ማሸነፍ ለማንም ሃይል ከቶ አይቻለዉም:: ጠንካራ ኢኮኖሚ ያለዉ በማናቸዉም ቀዉስ ወቅት ራሱን አረጋግቶ የሚያስተዳድርበት የዳበረ የማህበራዊና አስተዳደራዊ እሴት ባለቤት ነዉ:: የሕዝብ ብዛቱም ሆነ በሀገር ዉስጥና በዉጭ በሁሉም የአለም ሀገራት ተሰራጭተዉ ያሉ የተማሩ ልጆቹና ከሥር እየመጣ ያለዉ ትንታግ ትዉልድ ለሲዳማ ነፃነትና የሲዳማ ማንነታዊ ክብሩን ለማስጠበቅ ለምንም ለማንም ሃይል ተጽዕኖና ጫና ግንባራቸዉን አሳልፈዉ የሚሰጡ ናቸዉ:: አቶ ደሴ እዉነት ወይስ ሐሰት?? የምታዉቀዉን እዉነታ ያለመመስከሩ እንጂ እዉነታዉን መመስከሩ በሰማይም በምድርም ሃጢአት አይደለም::

አቶ ደሴ አንድ እዉነታ ብቻ ላንሳና ልሰናበትህ ይሄዉም ላለፉት 22 አመታት በሲዳማ ላይ በሲዳማ ታሪክ ታይቶ የማይታወቅ ጭፍጨፋ ጅምላ እስራትና አፈና የኢኮኖሚ ድቀት ወዘተ

ሴራዎችና እርምጃዎች በመንግስት ይሁን በግል አይታወቅም ተፈጽመዋል:: እየተፈጸሙም ነዉ:: ይህ ሁሉ እየተደረገ ያለዉ በተሳሳተ ግምት ሲዳማን በሁሉም ዘርፍ በማዳከምና በማሽመድመድ የገነትትዋን ሲዳማ ሀብትና ንብረት ያለ ተቀናቃኝ ለመዝረፍና የምድርቱ ባለቤት ለመሆን ነዉ:: ሆኖም ግን እስካሁን እየተደረገ ያለዉ ጫና በተቃራኒዉ ሕዝቡን እያጠነከረዉና ወደ ነፃነት ትግሉ እንድቀላቀል እያደረገዉ ነዉ:: ሕወሃት ብሶት የወለደዉ ትግል ዉጤት ነኝ ይል የለም ወይ?? እዉነትም ብሶት የወለደዉ:: እስራኤሎችም ጠንካራ የሆኑት በደረሰባቸዉ በደል አይደለምን?? ስለሆነም አቶ ደሴ እንዲያዉም ጫናዉ ከበፍቱ የበለጠ ቢቀጥል የሲዳማን የነፃነት ጉዞዉን ያፋጥንለታል::

አበቃሁ:: ቸር እንሰንብት:: ለማንነቴ አትጨነቅ:: አንድ ቀን ከእለታት አንድ ቀን ማንነቴን በገሃድ አሳዉቅህ ይሆናል::